# የማረጋገጫ ፍንጭ



ዊልያም ሙትሌ ማሴትላ ፋውንዴሽን

# የማረጋገጫ ፍንጭ

በዊሊያም ሙትሌ ማስቴላ ተቋም

**Development Learning Press**
Royal Palm Beach, Florida

**የማረጋገጫ ፍንጭ**
Breezes of Confirmation

**ተዘጋጀ:- በዊሊያም ሙትሌ ማስቴላ ተቋም**
William Mmutle Masetlha Foundation

**አሳታሚ:- ዴቬሎፐመንት ለርኒንግ ፐሬስ፤ሮያል ፖልም ቢች፤ፍሎሪዳ**
Development Learning Press-Royal Palm Beach-Florida

**ይህ መጽሀፍ ለዊልያም ሙትሌ ማስቴላ ፋዉንዴሽን በካሬን ጀሰን ፖሎክ ተጽፎ በቱ ዊንግስ ፋዉንዴሽን የገንዘብ ድጋፍ ታተመ:: መጽሀፉ ከካሬል ጋለሪ ማጂክ ምስሎችን አካቷል::እነዚህም ምስሎች በአሜሪካ፣በካናዳ፣እና በሌሎች ቦታዎች በኮፒ ራይት ህግ የተጠበቀ ሆኖ በፈቃድ ተጠቅመንበታል::**

**ትርጉም:- ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ በሳብሪ የልማት ተቋም**
**ሚያዝያ 2004 ዓ.ም አዲስ አበባ**
**ፓ.ሣ.ቁ 102 አዲስ አበባ**

Copyrigth © **የአዘጋጁ መብት የተጠበቀ ነው::**

## ስለዚህ ህትመት

ደቨሎፐመንት ለርኒንግ ፕሬስ (DLP)የደቨሎመንት ለርኒንግ አሶሴሽን (DLA) አባል ነው ። ይህ ማኅበር የተዋቀረው በአለማችን ላይ ቁጥራቸው በየጊዜው እየተበራከተ የመጣውና ፕሮጄዎቻቸው ስልጣኔን በሚያራምዱ ድርጅቶች ነው ። DLA እነዚህ ድርጅቶች የሚሰሩበትን መዋቅር( ፍሬምወርክ) ይሰጣል፤ በመካከላቸው ያለውን መስተጋብር፣ የሀሳብና የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። እንደነዚህ አባል ድርጅቶች ይህ ድርጅትም ለግለሰብ፣ ማኅበረሰብና ተቋማት እድገት መፋጠን የሚረዱ መንፈሳዊና ሳይንሳዊ ጽሁፎችን በማሳተምና በማሰራጨት ስራ ላይ የተሰማራ ነው።
እያንዳንዱ ህትመት በ DLPና የመማሪያ ጽሁፎቹ በፈለቁበት የጋራ ጥረት ላይ የተመሰረተ ነው።

ይህ “የማረጋገጫ ፍንጭ” የሚለው መጽሀፍ ለታዳጊ ወጣቶች ስልጠና ተብለው ከተዘጋጁት ጽሁፎች መካከል አንደኛው ነው ። ይህ ጽሁፍ ዊሊያም ሙትል ፋውንዴሽንና የ DLA አንድ አባል የጥረት ውጤት ሲሆን የተዘጋጀውም በዛምቢያ አገር በገጠር አካባቢ የሚገኙ ታዳጊ ወጣቶችን አቅም ለማጎልበት ና ከልጅነት ወደ ወጣትነት ለሚደረገው አስቸጋሪ የሽግግር ወቅት ለማዘጋጀት ታስቦ ነው። የፋውንዴሽኑ እንቅስቃሴ በዚህ አገር ውስጥ ሁለት አስርተ አመታትን አስቆጥሯል። በተለያዩ የልማት ዘርፎች ጤናንና ትምህርትን ጨምሮ ስልታዊ በሆነ መንገድ ለዛምቢያ ህዝቦች ቁሳዊና መንፈሳዊ እድገት አስተዋጽዎ በማድረግ ላይ ይገኛል ።

**መግቢያ**

ታዳጊ ወጣቶች ያለችግር ማንበብ እንዲችሉና የተወሰነ የቋንቋ እድገት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ከተፈለገ በርካታ መጽሀፍቶችን ማግኘት ይገባቸዋል ። የማረጋገጫ ፍንጭ " ብሪዝስ ኦፍ ኮንፊርሜሽን" የሚለው መጽሀፍ በዊሊያም ሙትል ፋውንዴሽን የተዘጋጀው ይህንን ታሳቢ በማድረግ ነው። ይህ ጽሁፍ ሲዘጋጅ ታዳጊ ወጣቶች (እድሜያቸው ከ12-15 አመት የሆናቸው) ሀሳባቸውን የመግለጽ ሀይል ለማሳደግ እንዲያስችል ከተዘጋጁት ጽሁፎች መካከል አንደኛው ሆኖ እንዲያገለግል ታስቦ ነው።
ይህ "የማረጋገጫ ፍንጭ" ስልጠናውን በሚወስዱት ታዳጊ ወጣቶች ላይ ሀሳባቸውን በትክክልና ግልጽ በሆነ መንገድ እንዲናገሩና ወደፊት ለሚያነቧቸው ከበድ ያሉ መጽሀፍትን ለመረዳት የሚያስችሉ ክህሎቶችን ለማዳበር ይረዳችዋል ተብሎ ይገመታል።

ከዊሊያም ሙትል ፋውንዴሽን ጋር አብረው የሚሰሩ ድርጅቶች በሙሉ የሰው ተፈጥሮ ቁሳዊና መንፈሳዊ ጎኖች እንዳሉት የሚያምኑ ናቸው። በቋንቋ የትምህርት ዘርፍ ለታዳጊ ወጣቶች የሚያዘጋጁትም ጽሁፎች በማንኛውም ደረጃ ጥረት የሚያደርገው÷ ውሳኔያቸውንና ተግባራቸውን የሚመራውን የግብረገባዊ መዋቅሮችን ለመፍጠር እንዲችሉና በሚያድጉበትም ጊዜ በሳል አዋቂዎችና በማኅበረሰባቸው ለውጥ ሂደት ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማስቻል ነው። ይህን ለማድረግ መጽሃፉ የስነ-ምግባር ጽንሰ ሀሳቦችን ለማስተላለፍና አስመስጋኝ የሆኑ አመለካከቶችን ለመገንባትና ፍሬያማ ህይወትን ለመምራት እንዲያስችል ታስቦ የተዘጋጀ ነው ። "የማረጋገጫ ፍንጭ" ለረጅም የትምህርት ሂደት እንደ ጥሩ ጅማሬነት ሊወሰድ ይችላል ። አንዲት ሙሶንዳ ስለምትባልና እድሜዋ 13 የሞላት ታዳጊ ወጣት÷ በትምህርት ቤት ዝግ እሷን ለመጠየቅ ስለመጣች ሮዝ ስለምትባል የአክስቷ ልጅ ታሪክ ይተርካል።
ከሙሶንዳ ወንድም ጎድዊንና የእሱ ጓደኛ የሆነው ቺሽምባ ጋር በመሆን ስለ ወደፊት ተስፋቸውና ስለሚኖሯቸው በርካታ አማራጮች ይወያያሉ። የታሪኩ መድብል ጥረት ማድረግና ከእግዚአብሄር ማረጋገጫን ማግኘት ነው። ታዳጊ ወጣቶች ግሩም የሆኑ ግብረገባዊ ማመዛዘንን ሊያዳብሩ ከሚችሉበት በርካታ መድብሎች ውስጥ አንደኛው ነው።

መጽሃፉ አስራ አራት ትምህርቶች አሉት። እያንዳንዱ ትምህርት አጫጭር ምንባቦች ሲኖሩት የመረዳት ችሎታን የሚያሳድጉ በርካታ ተከታታይ መልመጃዎችን ያካተተና የቋንቋ ክህሎቶችን የሚያሳድግ ነው። በቃል የሚጠኑ ጥቅሶች፤ መዝሙሮችና የመወያያ ጥያቄች በተለያዩ የትምህርት ክፍሎች ውስጥ ተሰራጭተው ይገኛሉ። ጽሁፉ መደበኛ ባልሆነ (በቱቶሪያል)መንገድ ቢሰጥ ይመረጣል። ቱቶሪያል ማለት በትንንሽ ቡድኖች ሆኖ በሰለጠነ አስጠኚ ዕርዳታ አማካኝነት የሚካሄድ ነው ።

በመጽሀፉ ውስጥ ያሉት ምንባቦች በቃላት አደረጃጀታቸውና ፍሰታቸው በተወሰነ ደረጃ ቀላል የሆኑና ይህንንም የጠበቁ ናቸው፡፡ ሆኖም ግን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከበድ ያሉ ቃላትና ሀረጎችን እንዲያካትት ተደርጓል፡፡ ከምንባቡ ውስጥ እነዚህን ከበድ ያሉ ቃላት በማውጣት ከምንባቡ ውጭ በሆኑ ሰፊ ሁኔታዎች ውስጥ ተጠቅሟል፥ እንዲሁም መልመጃዎች አሉት፡፡ በዚህ ሁኔታ ሰፋ ያሉ ቃላትን ለመጠቀም በመሞከር ታሪኩ ልክ ለህፃን የተዘጋጀና ጥልቀት የሌለው እንዳይመስል አድርጎታል፡፡ ከታዳጊ ወጣቶች ጋር የሚሰሩ ሰዎች መረዳት የሚገባቸው ታዳጊ ወጣቶች ህፃናት አለመሆናቸውንና ለጋ አእምሮአቸው በእየጊዜው እያደገ በመጣ ቁጥር በርካታ ነገሮችን የማወቅ ጉጉታቸው እየጨመረ እንደሚመጣ ነው፡፡

# ትምህርት 1

## ሙሶንዳን እንተዋወቃት

አስጠኛችሁ ታሪኩን ስታነብላችሁ/ሲያነብላችሁ በደምብ ተከታተሉ፡፡
አዲስ ወይም አስቸጋሪ ሆኖ ያገኛችሁትን ቃል ከስሩ አስምሩበት፡፡

---



ሙሶንዳ በቅርቡ አስራ ሶስት አመቷን ደፍናለች፡፡ ልቧ በደስታ ተሞልቷል፡፡ ሙሶንዳ ሁለት ወንድሞችና ሁለት ታናናሽ እህቶች አሏት፡፡ እህቶቿን መንከባከብ፥ አብራቸው መጫወትና እንዲ ስቁ ማድረግ ያስደስታታል፡፡ የምትኖረውም ከቤተሰቦቿ ጋር ሲሆን ቡሚ በምትባል በአንድ ትንሽ መንደር ውስጥ ነው፡፡ ወላጆቿ ወ/ሮ ሙሲንጋና አቶ ሙሲንጋ ይባላሉ፡፡ ሙሶንዳ ዛሬ በደስታ ፈንድቃለች፥ ምክንያቱም የአክስቷ ልጅ ሮዝ ለጥቂት ሳምንታት አብራቸው ለማሳለፍ ትመጣለች፡፡ ሙሶንዳና ሮዝ ጥሩ ወዳጃሞች ናቸው፡፡ አንዳቸው ለሌላቸው፣የሚያስቡትን ነገር ማካፈል ያስደስታቸዋል፡፡

### ተግባር 1

አስጠኛችሁ የጥናት ቡድኑን በጥንድ በጥንድ ትከፍላችኋለች/ይከፍላችኋል፡፡ በየተራ አንዳችሁ ለሌላችሁ ጥሩ አድርጋችሁ አንብቡ፡፡

### ተግባር 2

አስጠኛችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡ ጥያቄዎቹ ላይ ከተወያ ያችሁ በኋላ መልሱን በየግላችሁ ፃፉ፡፡

1. ሙሶንዳ ስንት አመቷ ነው?

______________________________

2. መንከባከብ የሚያስደስታት ማንን ነው?

______________________________

3. ከእህቶቿ ጋር ምን ታደርጋለች?

_______________________________________________

4. የምትኖረው የት ነው?

_______________________________________________

5. ወ/ሮ ሙሲንጋና አቶ ሙሲንጋ እነማን ናቸው?

_______________________________________________

6. ሙሶንዳ ዛሬ ለምን በደስታ ፈነደቀች?

_______________________________________________

7. ሮዝ ከእነ ሙሶንዳ ቤተሰብ ጋር የምታሳልፈው ጊዜ ምን ያህል ነው?

_______________________________________________

8. ሙሶንዳና ሮዝ የሚያስደስታቸው ምንድን ነው?

_______________________________________________

## ተግባር 3

ከታች የተሰጡትን ቃላትና ሀረጎች በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን እንድትሰሩ አስጠኛችሁ ትጠይቃችኋለች/ ይጠይቃችኋል፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ቤተሰብ | መንደር | መሳቅ | በደስታ | የአክስት ልጆች |
| በጫወታ | ትንሽ | ልቤ | ሀሳቦች | በደስታ መፈንደቅ |

## ተግባር 4

ከላይ የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች አሟሉ፡፡

1. ልጆች ትምህርት ______________________ መልክ ቢቀርብላቸው በቀላሉ መማር ይችላሉ፡፡
2. እናቴ የተደሰተች መሆኗን የማውቀው ______________________ ስትጀምር ነው፡፡
3. አባቴ÷ እናቴ÷ ወንድሞቼና እህቶቼ እኔንም ጨምሮ በአንድ ላይ ______________________ እንባላለን፡፡

4. ሙሰንዳ የምትኖረው በከተማ ሳይሆን በአንድ ትንሽ _________________________ ውስጥ ነው፡፡

5. እናቴ አንድ እህት አላት፥ የእርሷ ልጆች ለእኔ_______________________ ናቸው፡፡

6. አይጠመጎጥ ___________________ እንሳሳ ናት፡፡

7. ከጓደኞቼ ጋር ስጫወት _________________________________ በደስታ ይሞላል፡፡

8. ሮዝ ሁል ጊዜ እንደሳቀች ነው፥ ምክንያቱም ______________________ የተሞላች ስለሆነች ነው፡፡

9. አባታቸው ተረት ሊነግራቸው መሆኑን ሲያውቁ ልጆቹ _______________________ ይጀምራሉ፡፡

10. መልካም የሆኑ ______________________ ካሉን መልካም ነገሮችን እናደርጋለን፡፡

## ተግባር 5

ሙሰንዳን አስመልክቶ አንድ ወይም ሁለት አረፍተ ነገሮችን ፃፉ፡፡

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

# ትምህርት 2

## ሮዝን አውቶቡስ ተራ መቀበል

አስጠኛችሁ ታሪኩን ስታነብላችሁ/ሲያነብላችሁ በደምብ ተከታተሉ::
አዲስ ወይም አስቸጋሪ ሆኖ ያገኛችሁትን ቃል ከስሩ አስምሩበት::

---

ሮዝ አስራ አምስት አመቷ ነው :: ሙሶንዳ የሮዝን መምጣት በጉጉት እየተጠባበቀች ነው:: ሮዝን የምትጠይቃት በርካታ ጥያቄዎች አሏት:: በህይወቷ ውስጥ ምን ማድረግ እንደሚገባት ለመጠየቅ እያሰበች ነው::



ሮዝ በአውቶቡስ ወደ ቡሚ እየተጓዘች ነው:: ከቀትር በኋ ላ ሙሶንዳ ከአባቷ ጋር በመሆን ሊቀበሏት የቡሚ አውቶ ቡስ መናኸሪያ ድረስ ሄዱ:: ሮዝ ከአውቶቡሱ ልክ ስትወር ድ ሙሶንዳ አይኗን በሰፊው ከፍታ በመመልከት “ሮዝዬ!” በማለት ጮክ ብላ ተጣራች:: ሮዝም ጥሪውን ሰምታ ዘወር ስትል ሙሶንዳን ተመለከተቻት:: አንዳቸው ወደ ሌላቸው በመሮጥ ከተገናኙ በኋላ ተቃቅፈው ለረጅም ጊዜ ሰላምታ ተለዋወጡ:: በመቀጠል ከአቶ ሙሊንጋ ጋር ሰላምታ ተለዋወጠች:: አቶ ሙሊንጋ የሮዝን ሻንጣ በእጃቸው አንጠንጥለው ሶስቱም ወደ ቤታቸው ተጓዙ::

እቤት ሲደርሱ ወ/ሮ ሙሊንጋ እሳት ላይ ድስት ጥደው ለእራት የሚሆን ምግብ እያበሰሉ ነበር:: የሙሶንዳ ታናናሽ እህቶችና ታናሽ ወንድም ሮዝን ለመቀበል ከቤት ውስጥ እየሮጡ ወጡ:: ሲገናኙ ደስታና ሳቅ ሆነ:: “እንደራበሽ እርግጠኛ ነኝ” አሉ ወ/ሮ ሙሊንጋ ትንሽ ቆይ ተው:: “ለየት ያለ ምግብ አዘጋጅቻለሁ::”

“አዎን እውነትሽን ነው!” አለች ሮዝ:: “የሚንተከተከው ዶሮ ወጥ ይሸተኛል:: አውቶቡስ ውስጥ አልበላሁም:: አንድ ትንሽ ልጅና እናቱ አጠገቤ ተቀምጠው ነበር:: ትንሽ እንደተጓዝን ልጁ የሚበላ ስጭኝ በማለት እናቱን ጠየቀ:: እናቱ ምንም የሚበላ ነገር አለመያዟን ስለተረዳሁ ይዤ የነበረውን ዳቦ ሰጠኋት::”

**ተግባር** 1

**አስጠኛችሁ የጥናት ቡድኑን በጥንድ በጥንድ ትከፍላችኋለች/ይከፍላችኋል፡፡ በየተራ አንዳችሁ ለሌላችሁ ጥሩ አድርጋችሁ አንብቡ፡፡**

**ተግባር** 2

**አስጠኛችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡ ጥያቄዎቹ ላይ ከተወያያችሁ በኋላ መልሱን በየግላችሁ ፃፉ፡፡**

1. **ሮዝ ስንት አመቷ ነው**?

_______________________________________________

2. **ሙሰንዳ በጉጉት ትጠባበቀው የነበረው ማንን ነበር**?

_______________________________________________

3. **ሙሰንዳ ስታስብ የነበረው ስለምንድን ነበር**?

_______________________________________________

4. **ሮዝ ወደ ቡሚ በምን ተጓዘች**?

_______________________________________________

5. **ሙሰንዳና አባቷ ሮዝን የት ተቀበሏት**?

_______________________________________________

6. **ሮዝ ከአውቶቡሱ ላይ ልክ ስትወርድ ተመልክታ ሙሰንዳ ምን አደረገች**?

_______________________________________________

7. **ሮዝና ሙሰንዳ ሲገናኙ ምን አደረጉ**?

_______________________________________________

8. **የሮዝን ሻንጣ ማን አንጠለጠለው**?

_______________________________________________

9. **እነ ሮዝ ቤት ሲደርሱ ወ/ሮ ሙሊንጋ ምን እያደረጉ ነበር**?

_______________________________________________

10. ሮዝን ለመቀበል ከቤት ውስጥ እየሮጡ የወጡት እነማን ነበሩ?

---

11. ሮዝ እንደራባት ወ/ሮ ሙሲንጋ ለምን እርግጠኛ ሆኑ?

---

12. ሮዝ እርቧት የነበረው ለምንድን ነበር?

---

## ተግባር 3

አሁን ደግሞ አስጠኛችሁ መልመጃዎችን እንድታነቡና ትክክለኛውን መልስ እንድታከቡ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡

1. ሙሰንዳ የሮዝን መምጣት "በጉጉት ትጠባበቅ" ነበር፡፡ ይህ ማለት

   ሀ. ሙሶንዳ መስኮት ከፍታ ወደ ውጭ እያየች ነበር፡፡

   ለ. ሙሶንዳ ሮዝ ምን እንደምትመስል ማስታወስ አልቻለችም፡፡

   ሐ. ሮዝን ለማየት በጣም ናፍቃ ነበር፡፡

2. በህይወቷ ውስጥ ምን ማድረግ እንደሚገባት ሙሶንዳ ስታስብ ነበር፡፡ ይህ ማለት ስታስብ የነበረው

   ሀ. ጤነኛ እንድትሆን መመገብ ስላለባት የምግብ አይነቶች ነው፡፡

   ለ. ስታድግ ምን መሆን እንደሚገባት ነው፡፡

   ሐ. በሚቀጥለው ቀን ምን ማድረግ እንደሚገባት ነው፡፡

## ተግባር 4

ከታች የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን እንድትሰሩ አስጠኚያችሁ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ጥያቄዎችን | አስባለሁ | መጓዝ | አቀፈችው | ህይወት |
| የደረሰችው | ርቦታል | ተከፍቶ | ሰላምታ ይለዋወጣል | ልዩ |

## ተግባር 5

ከላይ የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች አሟሉ::

1. ሰዎች በእግር ወይም በአውቶቡስ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ______________________ ይችላሉ::
2. እናትየው ልጇ ሲወድቅ አይታ እሮጣ በመድረስ ከመሬት አንስታ ____________________ ::
3. ልጆቹ ለመማር ስለፈለጉ አስተማሪዋ በርካታ _________________________ ጠየቀቻቸው::
4. እናቴ ለራታችን የሚሆን ___________________ ምግብ አዘጋጅታለች ::
5. አባቴ ቀኑን በሙሉ ከባድ ስራ ሲሰራ ስለዋለ በጣም ________________________________::
6. መጋዘኑ ሰኞ ዕለት ____________________________________________ ስራውን ይጀምራል::
7. ወደ ሱቁ  ከሚመጡ ሰዎች ጋር በሙሉ ሞቅ ያለ ________________________________ ::
8. ወደፊት ስለማደርጋቸው ነገሮች ከወዲሁ __________________________________________ ::
9. ከተማሪዎቹ መካከል በስብሰባው ላይ ለመገኘት መጀመሪያ __________________________ ከሪማ ነች::
10. የሙሰንዳ ___________________________________________በደስታና በሳቅ የተሞላ ነው::

## ተግባር 6

በዚህ ትምህርት ውስጥ ከተማራችሁት ሁለት ወይም ሶስት አረፍተ ነገሮችን ስሩ::

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

## ተግባር 7

ከታች የተሰጡትን ጥያቄዎች ከጓደኛችሁ ጋር በመሆን ከተወያያችሁ በኋላ ጥቅሱን በማጥናት በቃል ያዙ::

**“ . . .በመንገዳችሁ ለሚያጋጥማችሁ በሙሉ ልባችሁ በፍቅራዊ ደግነት ይንደድ ::”**

1. በፍቅራዊ ደግነት መንደድ ያለበት ምንድን ነው?

_______________________________________________________________________________

2. ልባችሁ ምን ማድረግ አለበት?

---

3. ፍቅራዊ ደግነት የምናሳየው ለማን ነው?

---

4. ለማናውቀው ሰው ፍቅራዊ ደግነት ማሳየት ይገባናል?

---

# ትምህርት 3

# እራት

**አስጠኛችሁ ታሪኩን ስታነብላችሁ/ሲያነብላችሁ በደምብ ተከታተሉ።
አዲስ ወይም አስቸጋሪ ሆኖ ያገኛችሁትን ቃል ከስሩ አስምሩበት።**

---

ሙሶንዳ ሳህኖችና ኩባያዎች ስታቀርብ፥ ወ/ሮ ሙሲንጋ ዶሮ ወጡን አቀረቡ። እራታችውን እየበሉ ስለ ሮዝ ቤተሰቦች በአጠቃላይና እያንዳንዳቸው ምን እያደረጉ እንደሆነ አወጉ።

እራቱ ካበቃ በኋላ ሙሶንዳና ሮዝ የተበላበትን ሳህን አጠቡ። ሙሶንዳ ሮዝን እንደዚህ ስትል ጠየቀቻት "ሳድግ ምን መሆን እንደሚገባኝ ትመክሪኛለሽ?"

" ሁልጊዜ እኔም እራሴን የምጠይቀው ይሄንኑ ነው።" አለች ሮዝ። ሙሶንዳም እንዲህ በማለት ስለራሷ ገለጸች "ግልጋሎት ለመስጠት አስባለሁ። ሌሎች ሰዎችን ሊረዳ የሚችል አንድ ነገር ማድረግ እፈልጋለሁ። ነርስ መሆን እፈልጋለሁ፥ ነገር ግን ጠንክሬ ማጥናት አለብኝ። ከፍሎ ለመማርም ይወደድብኛል፥ ወላጆቼ ለዚህ የሚሆን በቂ ገንዘብ ይኖራቸዋል ብዬ አላስብም።"



"ያልሽው እርግጥ ነው! ነገር ግን መሞከር አለብሽ" አለች ሮዝ። "አንድ ቃል አለ "ማረጋገጫ" ይባላል ። ይህን ቃል ከጥቂት ሳምንታት በፊት በክፍሌ ውስጥ ተማርኩት። አስተማሪያችን የነገረን ነገር እግዚአብሄር እንደሚያረጋግጥልንና እንደሚረዳን ነው። አሁን ይህን ቃል እጅግ በጣም ወድጄዋለሁ። ነርስ ለመሆን ልብሽን ካነሳሳሽው ማረጋገጫ ከእግዚአብሄር እንደምትቀበይ እርግጠኛ ነኝ።" በማለት አክላ ነገረቻት።

## ተግባር 1

አስጠኛችሁ የጥናት ቡድኑን በጥንድ በጥንድ ትከፍላችኋለች/ይከፍላችኋል። በየተራ አንዳችሁ ለሌላችሁ ጥሩ አድርጋችሁ አንብቡ።

## ተግባር 2

**አስጠኛችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል:: ጥያቄዎቹ ላይ ከተወያያችሁ በኋላ መልሱን በግላችሁ ፃፉ::**

1. ቤተሰቡ አብረው እየተመገቡ ሳለ ምን አደረጉ?

_______________________________________________

2. ሮዝና ሙሰንዳ እራት በልተው ከጨረሱ በኋላ ምን አደረጉ?

_______________________________________________

3. ሙሰንዳ ሮዝን የጠየቀቻት ጥያቄ ምን ነበር?

_______________________________________________

4. ሙሰንዳ ወደፊት ምን ለመሆን ትፈልጋለች?

_______________________________________________

5. ነርስ ለመሆን የፈለገችው ለምንድን ነው?

_______________________________________________

6. የነርስነትን ሞያ ላትማር የምትችልበትን ምክንያት ለምን አሰበች?

_______________________________________________

7. ሮዝ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የተማረችው አዲስ ቃል ምን ነበር?

_______________________________________________

## ተግባር 3

**አሁን ደግሞ አስጠኛችሁ መልመጃዎችን ታነብላችሁ/ያነብላችሁና ትክክለኛውን መልስ እንድታከቡ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል::**

1. “ ማረጋገጫ ” የሚለው ቃል ትርጉም

ሀ. ነገሮችን ከማድረግ የሚያግደን ነገር

ለ. የምናደርገው ነገር ትክክል መሆኑን እንድናውቅ የሚረዳን ነገር

ሐ. ነገሮችን በፍጥነት ለማከናወን የሚረዳን ነገር

2. ሙሰንዳ ነርስ ለመሆን " ልቧን አነሳሳች " ይህ ማለት

ሀ. ነርስ የመሆን ሀሳቧን ሰረዘች

ለ. ነርሶችን ትፈራለች

ሐ. ነርስ ለመሆን ስሜቷን አነቃቃችው

## ተግባር 4

ከታች የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን እንድትሰሩ አስጠኚያችሁ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ማብራራት | አስተናገዱ | በአንድነት | ደስተኛ | ሳምንት |
| በማጥናታቸው | ነርሷ | የሚማረው | አስተማሪ | ተቀበለች |

## ተግባር 5

ከላይ የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች አሟሉ፡፡

1. ወ/ሮ ሙሊንጋ የሰሩትን ዶሮ ወጥ እራት ላይ ______________________________ ፡፡
2. ነገሮችን ___________________________________ ስንሰራ በተሻለ ፍጥነት እናጠናቅቃለን፡፡
3. ትምህርት በአንድ _________________________________________ ጊዜ ውስጥ ይጀመራል፡፡
4. ጥሩ ዜና ስትሰማ _________________________________________________________ ሆነች፡፡
5. ታላቅ ወንድሜ _____________________________________ ከተማ ውስጥ ነው፡፡
6. የታመሙትን ሰዎች ለማከም ____________________ ወደ አካባቢው መንደሮች በየሳምንቱ ትጓዛለች ፡፡
7. ጥሩ ______________________________ ተማሪዎቹ አዳዲስ ነገሮችን እንዲማሩ ይረዳቸዋል፡፡
8. ጥሩ አስተማሪ ነገሮችን በጥሩ ______________________________________ የሚችል ነው፡፡
9. ከአክስቷ ልጅ የተላከላትን ረዥም ደብዳቤ ትላንትና ____________________________ ፡፡
10. ልጆቹ አዲስ መዝሙር _________________________________________ ተደስተው ነበር፡፡

**ተግባር** 6

**በታሪኩ ውስጥ ሙሶንዳ ነርስ ለመሆን እንደምትፈልግ አንብበናል ። እናንተ ምን መሆን እንደምትፈልጉ የሚገልጽ አንድ አንቀጽ ፃፉ ።**

# ትምህርት 4

# የምሽት ሽኩሽክታ

***አስጠኛችሁ ታሪኩን ስታነብላችሁ/ሲያነብላችሁ በደምብ ተከታተሉ።። አዲስ ወይም አስቸጋሪ ሆነው ያገኛችሁትን ቃል ከስሩ አስምሩበት።።***

*በዚያን ቀን ምሽት መኝታቸው ውስጥ ገብተው ሳለ ሙሶንዳ ለሮዝ በሹክሹክታ እንዲህ ስትል ጠየቀቻት “ሮዚ÷ “ማረጋገጫ” የሚል ቃል ተናግረሽ ነበር” ይህ ማለት የቻልኩትን ያህል በትምህርቴ ጠንክሬ ካጠናሁ እግዚአብሔር የነርስነትን ሙያ የምማርበት ገንዘብ ይሰጠኛል ማለት ነው?”*

*ሮዝ ወደ ሙሶንዳ በመዞር አይኗን ተመለከተችና “እንደዛ ማለቴ አይደለም÷ ለማለት የፈለኩት ነገሮችን እንሞክርና ሊከፈቱ የሚችሉ በሮችን እንይ ነው።። እኔ የማውቀው ነገር እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ተሰጥዎችን ሰጥቶናል።። ፈልገን ማግኘትና እንዴት መጠቀም እንዳለብን መማር የእኛ ድርሻ ነው።።” በማለት ሮዝ መለሰችላት።።*

*“ተሰጥዖዎችሽ ምን እንደሆኑ ታውቂያቸዋለሽ?” ብላ ሙሶንዳ ጠየቀቻት።።*

*“ እርግጠኛ አይደለሁም÷ ነገር ግን ብዙ ነገሮችን ማድረግ እወዳለሁ።። ለምሳሌ፤ግጥሞችን መፃፍና ዳንቴል መስራት።። ከሁሉም በላይ የምወደው ግን ከልጆች ጋር መሆን÷ አብሬያቸው መጫወትና እንዲማሩ መርዳት ነው።። ብቻ ... አስተማሪ ብሆን ደስ የሚለኝ ይመስለኛል።።” በማለት ሮዝ መለሰችላት ።።*



*ሙሶንዳ ሳቀች “አንቺ አስተማሪ ብትሆኚ ኖሮ በምታስተምሪው ክፍል ውስጥ ተማሪ ብሆን ምኞቴ ነበር።።” ካለች በኋላ በመስኮታቸው መስታወት ውስጥ አሻግራ በጨለማው ሰማይ ላይ ያሉትን ከዋክብቶች እየተመለከተች የድርጭት ወፍ ጩኸት ታዳምጥ ነበር ።። የእርሷ ተሰጥዖዎች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ታስብ ነበር።። በመቀጠል ጎዲዊን ስለሚባለው ታላቅ ወንድሟ አንስታ ለወደፊት ህይወቱ ምን ማድረግ እንደሚችል ማሰብ ጀመረች ።። በአራት አመታት ይበልጣታል÷ቀድሚትም ትልቅ ሰው ይሆናል።። ልጆች ሳሉ በጣም ይቀራረቡ ነበር።። አሁን ግን በሁለት የተለያዩ አለማት ውስጥ እንደሚኖሩያህል ነው የተራራቁት።። ያም ሆኖ ግን ጥሩ ወንድሜ ነው።።” ብላ በመጨረሻ ላይ ካሰበች በኋላ እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ወሰዳት።።*

**ተግባር** 1

**አስጠኛችሁ የጥናት ቡድኑን በጥንድ በጥንድ ትከፍላችኋለች/ይከፍላችኋል፡፡ በየተራ አንዳችሁ ለሌላችሁ ጥሩ አድርጋችሁ አንብቡ፡፡**

**ተግባር** 2

**አስጠኛችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡ ጥያቄዎቹ ላይ ከተወያያችሁ በኋላ መልሱን በግላችሁ ፃፉ፡፡**

1. **ሙሰንዳ ከመተኛቷ በፊት ሮዝን የጠየቀቻት ምንድን ነበር**?

______________________________________________

2. **የተናገረችው ጮክ ብላ ነበር**?

______________________________________________

3. **ሙሰንዳ ጥያቄ ስትጠይቃት ሮዝ ምን እያደረገች ነበር**?

______________________________________________

4. **እግዚአብሄር ለእያንዳንዳችን ስላደለን ተሰጥዖ ሮዝ ምን ተናገረች**?

______________________________________________

5. **ተሰጥዖዎቻችን ምን እንደሆኑ ካገኘን በኋላ ምን ማድረግ እንደሚገባን ሮዝ ምን አለች**?

______________________________________________

6. **ሮዝ ምን መሆን እንደምትፈልግ ተናገረች**?

______________________________________________

7. **ንግግራቸውን ካገባደዱ በኋላ ሙሰንዳ ምን አደረገች**?

______________________________________________

8. **ሙሰንዳ ስለማን እያሰበች ነበር**?

______________________________________________

9. **ጎዲዊን ስንት አመቱ ነው**?

______________________________________________

10. ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ሳይወስዳት በፊት ሙሶንዳ ስለምን ስታስብ ነበር?

___

___

## ተግባር 3

አሁን ደግሞ አስጠኛችሁ መልመጃዎችን ታነብላችሁ/ያነብላችሁና ትክክለኛውን መልስ እንድታከቡ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡

1. ሮዝ ለሙሶንዳ የነገረቻት ነገሮችን መሞከር እንዳለብንና “የሚከፈቱልን በሮች” ምን እንደሚሆኑ እንመልከት የሚል ነበር፡፡ ይህ ማለት

   ሀ. አንድ ነገር መሞከርና ማቆም ከዚያም ሌላ ነገር መሞከር ይገባናል፡፡

   ለ. የተለያዩ ነገሮችን መሞከርና እርግጠኛ የምንሆንባቸውንና የማንሆንባቸውን ነገሮች መለየት ያስፈልገናል፡፡

   ሐ. አንድን ነገር አንድ ቦታ ላይ ከሞከርን በኋላ እርሱን ትተን ሌላ ቦታ ሄደን ያንኑ ነገር መሞከር፡፡

2. ሙሶንዳና ወንድሟ ጎዲዊን የሚኖሩት “በተለያዩ አለማት” ውስጥ ነው፡፡ ይህ ማለት

   ሀ. የሚያስቡት የተለያየ ነው

   ለ. በእኩል እንድሜ ላይ አይገኙም

   ሐ. ወንድሟ የሚኖረው እሩቅ አገር ነው

## ተግባር 4

ከታች የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን እንድትሰሩ አስጠኚያችሁ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| በሽኩሽክታ | የምትችለውን | ወደፊት | ተሰጥዖዎች | ግጥም |
| ለመመለስ | ከዋክብት | ካዳመጥሽ | አላወቀችም | በትክክል |

## ተግባር 5

ከላይ የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች አሟሉ፡፡

1. እርሱ ________________ ለቤተሰቦቹ ቤት እንደሚሰራላቸው ተሰፋ አድርጓል፡፡

2. ሰማዩ በምሽት አምሯል፥ ምክኒያቱም ______________________ ሞልተውበታል፡፡

3. ልጆቻቸውን ከእንቅልፋቸው እንዳይቀሰቅሷቸው ስለፈለጉ ____________________ ማውራት ጀመሩ።

4. ልጆችን ማስተማር ከሮዝ ________________________________ አንዱ ነው።

5. እርሱ የተሰጠውን __________________________ በቃሉ አጥንቶ መናገር ቻለ።

6. በደምብ ________________________ የቤተክርስቲያኑ ቅዳሴ እዚህ ድረስ ይሰማል።

7. ጥሩና ጠንክራ የምትሰራ ተማሪ ስለሆነች የተሰጣትን ነገር በሙለ____________________ ያህል አሳምራ መስራት ያስደስታታል።

8. አስተማሪዋ አንድ ጥያቄ ስትጠይቅ፥ ተማሪዎቹ ________________ ይሽቀዳደማሉ።

9. ሁለቱ ትናንሽ ድመቶች ____________________________________ ይመሳሰላሉ።

10. እህቷ ማንበብ እንድትችል ምን ማድረግ እንደሚገባት _____________________ ።

## ተግባር 6

በታሪኩ ውስጥ ሮዝ እግዚአብሄር ለእያንዳንዳችን ተሰጥዎችን ሰጥቶናል ብላለች። የክፍል ጓደኞቻችሁ ያሏቸውን አምስት ተሰጥዎች ዘርዝሩ።

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

# ትምህርት 5

## ከራስህ በፊት ወንድምህን አስቀድም

አስጠኛችሁ ታሪኩን ስታነብላችሁ/ሲያነብላችሁ በደምብ ተከታተሉ፡፡
አዲስ ወይም አስቸጋሪ ሆነው ያገኛችሁትን ቃል ከስሩ አስምሩበት፡፡

---



በነጋታው ሙሶንዳና ሮዝ ለሽርሽር ከቤት ውጭ ለመውጣት ፈለጉ፡፡ በመጀመሪያ ግን ወ/ሮ ሙሊንጋን ቤት በማፅዳት ረዱ፡፡ የታጠቡትን ልብሶች እያሰጡ ሳለ ሮዝ አንድ መዝሙር መዘመር ጀመረች፡፡ ስለሌሎች ፍላጎቶች ማሰብ የሚል ውብ የሆነ መዝሙር ነበር፡፡ ስራቸውን በፍጥነት ካገባደዱ በኋላ ፀሐዩ ሳይበረታ በፍጥነት ወጥተው ሄዱ፡፡ እረጅም ርቀት ተጓዙ፡፡አንዳንዴ እያወሩ አንዳንዴም በዝምታ እየተዋጡ ነበር፡፡"በመንደራችን ውስጥ ያሉ ልጆች እርስ በርሳቸው የሚጣሉት ለምን ይሆናል ብለሽ ታስቢያለሽ?" ስትል ሙሶንዳ ሮዝን ጠየቀቻት፡፡

" አላውቅም፥ ነገር ግን ህፃን ስለሆኑ ብቻ አይመስለኝም፡፡ በአሁኑ ጊዜ በርካታ ህዝቦች እርስ በርሳቸው እየተዋጉ እንደሆነ እናውቃለን፡፡ በወጣቶች ቡድናችን ውስጥ ይህንን ጥቅስ አጥንተናል ፤*"የተፈጠራችሁት አንዳችሁ ለሌላችሁ ፍቅር እንድታሳዩ ነው... "*

" እውነትሽን ነው፡፡ " አለች ሙሶንዳ፡፡ በመቀጠል እንዲህ አለች "እና ዛሬ ጠዋት ስትዘምሪ የነበረው መዝሙር ከራሳችን በፊት ሌሎችን ማስቀደም ይገባናል የሚል ነበር፡፡"

" የመዝሙሩ ጥቅስ ደግሞ ከሌላ ጥቅስ ላይ የተወሰደ ነው፥ 'ከራሱ በፊት ወንድሙን ያስቀደመ የተባረከ ነው፡፡ '" አለች ሮዝ ፡፡

ለጥቂት ጊዜ ዝምታ ሰፈነ፥ በመቀጠልም ሙሶንዳ እንዲህ አለች "ይህ እውነት እንደሆነ ታውቂያለሽ፥ ከራሴ ይልቅ የማስቀድመው ወንድሜን እኮነው፡፡ እሱም ቢሆን ከራሱ በፊት የሚያስቀድመው እኔን ነው፡፡ በዚህ ምክንያት በሰላም እንኖራለን፡፡"

በድንገት ሙሶንዳ መሳቅ ጀመረች፡፡
"ለምንድን ነው የምትስቂው?" ስትል ሮዝ ጠየቀቻት፡፡
" ውድ ወንድሜ ከራሴ በፊት አንተን አስቀድማለሁ ብዬ ስነግረው" የጎዲዊን ፊት እንዴት እንደሚሆን እየታየኝ ነው፡፡

"ያ ቂልነት ይሆናል÷" አለች ሮዝ፡፡ "ምናልባትም ስለዚህ ጉዳይ ዛሬ ማታ በእራት ላይ አንስተን እንነጋገራለን፡፡ ማረጋገጫ የሚለውንም በድጋሚ አንስተን እንወያይ ይሆናል፡፡"

## ተግባር 1

አስጠኛችሁ የጥናት ቡድኑን በጥንድ በጥንድ ትከፍላችኋለች/ይከፍላችኋል፡፡ በየተራ አንዳችሁ ለሌላችሁ ጥሩ አድርጋችሁ አንብቡ፡፡

## ተግባር 2

አስጥኛችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡ ጥያቄዎቹ ላይ ከተወያያችሁ በኋላ መልሱን በግላችሁ ፃፉ፡፡

1. ሙሰንዳና ሮዝ ለሽርሽር ከመውጣታቸው በፊት ምን አደረጉ ?

_______________________________________________

2. ሮዝ ልብስ እያሰጣች ምን ታደርግ ነበር?

_______________________________________________

3. ሮዝ የምትዘምረው ስለምን ነበር?

_______________________________________________

4. በመንገድ ላይ እየሄዱ ሳለ ሙሰንዳ ሮዝን ስለምን ጠየቀቻት?

_______________________________________________

5. ሙሰንዳ ለጠየቀችው ጥያቄ ሮዝ ምን ምላሽ ሰጠች?

_______________________________________________

6. በወጣት ቡድን ውስጥ ሮዝ ያጠናችው ጥቅስ ምን የሚል ነበር?

_______________________________________________

7. መዝሙሩ ምን ከሚለው ጥቅስ የወጣ ነው?

_______________________________________________

8. ሙሰንዳ ከራሷ በፊት ወንድሟን ማስቀደሟና እርሱም እህቱን ማስቀደሙ በቤታቸው ውስጥ ምን ለውጥ እንዳመጣ አሰበች?

______________________________________________________________________

9. ሙሰንዳ ለምን መሳቅ ጀመረች?

______________________________________________________________________

## ተግባር 3

አሁን ደግሞ አስጠኛችሁ መልመጃዎችን ታነብላችሁ/ያነብላችሁና ትክክለኛውን መልስ እንድታ ከቡ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡

1. ሮዝ ጥቅሱን ለሙሰንዳ ከነገረቻት በኋላ "ለጥቂት ጊዜ" በዝምታ ተዋጡ ፡፡ ይህ ማለት

   ሀ. ሮዝና ሙሰንዳ ለጥቂት ሰዓታት አልተነጋገሩም፡፡

   ለ. ሮዝና ሙሰንዳ ለአንድ ወይም ሁለት ደቂቃዎች አልተነጋገሩም፡፡

   ሐ. ሮዝና ሙሰንዳ ለሁለት ሴኮንዶች አልተነጋገሩም፡፡

2. "ጉዳዩን አንስተን እንነጋገራለን" ማለት ጉዳዩ

   ሀ. ይዘረዘራል
   ለ. ማብራሪያ ይሰጥበታል
   ሐ. ይታሰብበታል

## ተግባር 4

ከታች የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን እንድትሰሩ አስጠኚያችሁ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| እመርጣለሁ | በመፍጠር | ውብ | በፍጥነት | መጣላትን |
| ልብስ | እርጭ | በድንገት | ጦርነት | ርቀት |

## ተግባር 5

ከላይ የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች አሟሉ፡፡

1. ልጆች መማር ያለባቸው መተባበርን እንጂ ____________________ አይደለም፡፡

2 ሁሉም አበቦች __________________ ናቸው፡፡

3. ንጹህ ________________ ሲለብስ ደስታ ይሰማዋል::

4. እሷ ዝናብ መዝነብ ሲጀምር _____________ ተራመደች::

5. _________________ በአለም ላይ ከፍተኛ የሆነ ሀዘን ያስከትላል::

6. እርሱ____________ ባለ ምሽት ከእንቅልፉ እየነቃ ቀን ስለሰራቸው ስራዎች ማሰብ ልምዱ አድርጎታል::

7. አያቱን ለመጠየቅ በየሳምንቱ ረዥም __________________ ይጓዛል::

8. ልጆች አዳዲስ ጨዋታዎችን _____________ መጫወት ይወዳሉ::

9. ከጥሬ ይልቅ የበሰለ ማንጎ መብላት __________________ ::

10. በሬዲዮ ዜና እያዳመጥን ሳለ ___________________ የቤታችን በር በሀይለኛ ተንኳኳ::

## ተግባር 6

ሮዝ ስትዘምር የነበረው መዝሙር ይህ ነበር:: አስጠኛችሁ ታስተምራችኋለች/ያስተምራችኋል::

**ወንድምህን አስቀድም**

**አዝማች:**

ወንድምን ማስቀደም መባረክ ነው::

እንደምትንከባከብ ማሳያ መንገድ ነው::

እህትህን ማስቀደም መባረክ ነው::

ስታካፍል ይበልጥ ትከብራለህ

ተጠምቻለሁ ተጠምቻለሁ

ነገርግን ወንድሜን አስቀድማለሁ

ስለሆነም ውሃውን እሰጠዋለሁ
እርሱም ጥሙን ያረካበታል::

(**አዝማች**)

ተርቤአለሁ ተርቤአለሁ

እህቴም እንደዚሁ

ስለሆነም ከምግቤ እሰጣታለሁ

ይህን ማድረግ ድንቅ ነው::

## ተግባር 7

ከታች የተሰጡትን ጥያቄዎች ከጓደኞችሁ ጋር በመሆን ከተወያያችሁ በኋላ ጥቅሱን በማጥናት በቃል ያዙት፡፡

**"የተፈጠራችሁት አንጻችሁ ለሌላችሁ ፍቅርን እንድታሳዩ ነው፡፡"**

1. ምን እንድናሳይ ነው የተፈጠርነው?

______________________________________________

2. ለማን ነው የምናሳየው?


______________________________________________

# ትምህርት 6

# ቺሽምባ

**አስጠኛችሁ ታሪኩን ስታነብላችሁ/ሲያነብላችሁ በደምብ ተከታተሉ፡፡**
**አዲስ ወይም አስቸጋሪ ሆነው ያገኛችሁትን ቃል ከስሩ አስምሩበት፡፡**

---



ጎዲዊን በጣም የሚቀርበው የክፍል ጓደኛ አለው፡፡ ስሙም ቺሽምባ ይባላል፡፡ወ/ሮ ሙሊንጋንና አቶ ሙሊንጋን ለመጠ የቅ ዘወትር ወደ ቤታቸው ይመጣል፡፡ዛሬ እራት የሚበላው አብሯቸው ነው፡፡ እራታቸውን እየበሉ ሳለ የሚያደርጉት ውይይት ከአንድ ርዕስ ወደ ሌላ ርዕስ ይዘል ነበር፡፡ሙሶንዳ ማረጋገጫ ስለሚባለው ርዕስ ማንሳት ስለፈለገች ትዕግስት አጥታለች፡፡ በስተመጨረሻ ለጥቂት ጊዜያት ፀጥታ ሰፍኖ ነበር፡፡ "ሮዝና እኔ ስለ ማረጋገጫ እየተነጋገርን ነበር፡፡" በማለት ሙሶንዳ ዝምታውን ሰበረች፡፡

"ታናሽ እህቴ ደግሞ ውይይቱን ቀጠለች፥" አለ ጎዲዊን ጉሮሮውን እያጸዳ፡፡ ያስደነቀው ደግሞ ቺሽምባ ለማዳመጥ ፍላጎት እንዳለው ሲመለከት ነበር፡፡

" ይህ ቃል ላንቺ ምን ትርጉም አለው?" ሲል ጎዲዊን ሙሶንዳን ጠየቃት፡፡

ሙሶንዳ በመደነቅ ሮዝን ተመለከተቻት፥ ለተጠየቀችው ምላሽ ትሰጥበታለች ብላ ተስፋ በማድረግ፡፡

"ማረጋገጫ ... በምናደርገው ነገር እግዚአብሄር ማረጋገጫን ይሰጠናል፥ ይረዳናልም፡፡" አለች ሮዝ ፡፡

ቺሽምባ ለጊዜው ምንም አልተናገረም፥ አይኖቹም በሀዘን ተሞሉ፡፡ "ከጥቂት ወራት በፊት" በማለት በዝግታ ማውራት ጀመረ፡፡ "አባቴ ከስራ ተባሯል፥ በስራው ታማኝና ሀላፊነት የሚሰማው ነው፡፡ ይህንንም እያንዳንዱ የመስሪያ ቤቱ ባልደረባዎች ያውቃሉ፡፡ ለአስራ ስምንት አመታት በአንድ ድርጅት ውስጥ በጥበቃ ሰራተኝነት አገልግሏል፥ በድንገት ከስራ አባረሩት፡፡ ምክንያቱን ሁላችንም አውቀናል፥ ለተጨማሪ ሁለት አመታት ቢያሰሩት የጡረታ ጊዜው ስለሚደርስና ድርጅቱም የጡረታ አበል መክፈል እንደሚገባው ስለሚያውቁ ነው፡፡ ያጠራቀምነው ገንዘብ የለንም፡፡ ለጊዜው ምንም እንኳን ታላቅ ወንድሜ እየረዳን ቢሆንም

የሚቀጥለው አመት ትምህርት ቤት የምገባ አይመስለኝም፣ ምክንያቱም ለቤት ኪራይና ለምግቤ መክፈል ስለማልችል፡፡ በእውነቱ መማር እወዳለሁ፡፡ እግዚአብሄር ለምን እንደማይረዳኝ ይገርመኛል፡፡”

ሁሉም ሰው ወደ አቶ ሙሲንጋ አቅጣጫ ተመለከቱ፥ ለጥያቄው መልስ ይሰጣሉ ብለው በመጠበቅ፡፡

አቶ ሙሲንጋ ፈገግ በማለት እንዲህ አሉ “አንድ ጥረት በምናደርግበት ጊዜ እግዚአብሄር ያረጋግጥልናል ማለት፣ ህይወት ቀላል ናት ማለት አይደለም፡፡ ህይወቶቻችሁ በሙሉ በችግር የተሞሉ ሊሆኑ ይችላሉ፥ አሳዛኝ ሁኔታው ደግሞ አብዛኛዎቹ የሚከሰቱት በፍትህ መታጣት ምክንያት ነው፡፡ ቢሆንም ግን ጠንክራችሁ መስራት ይኖርባችኋል፡፡ ለጊዜው ነገሮች የጠበቃችሁትን ያህል ባይሄዱላችሁም እንኳ የእግዚአብሔርን ማረጋገጫ ለማግኘታችሁ እርግጠኛ ሁኑ፡፡ በተለይም ፍትህ አልበኝነትን ለማስወገድ በምታደርጉት ጥረታችሁ ልዩ ማረጋገጫ ይሰጣችኋል፡፡” ወደ ቺሽምባ ፊታቸውን በመመለስ እንዲህ አሉ “ቤተሰባችሁ አንድነት ያለበትና ጠንካራ ሰራተኞች ናችሁ፡፡ ነገሮች እንደሚቀየሩላችሁ ልቦናዬ ይነግረኛል፡፡ እንደው ምን አለ በለኝ! ትምህርትህን ትጨርሳለህ፡፡”

## ተግባር 1

አስጠኛችሁ የጥናት ቡድኑን በጥንድ በጥንድ ትከፍላችኋለች/ይከፍላችኋል፡፡ በየተራ አንዳችሁ ለሌላችሁ ጥሩ አድርጋችሁ አንብቡ፡፡

## ተግባር 2

አስጠኛችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡ ጥያቄዎቹ ላይ ከተወያያችሁ በኋላ መልሱን በየግላችሁ ፃፉ፡፡

1. ቺሽምባ ማን ነው?

______________________________

2. ቺሽምባ ዛሬ ማታ ምን እያደረገ ነው?

______________________________

3. ሙሰንዳ መናገር የፈለገችው ስለ ምን ነበር?

______________________________

4. ጎዲዊን ለምን ተደነቀ?

5. ጎዲዊን ሙሶንዳን ምን ጠየቃት?

6. ሮዝ የጎዲዊን ጥያቄ እንዴት መለሰች?

7. የቺሽምባ አባት ለአስራ ስምንት አመታት ምን ሲሰሩ ነበር?

8. ለምን ከስራቸው ተባረሩ?

9. ለምድን ነው ቺሽምባ በሚቀጥለው አመት ትምህርት ቤት መግባት የማይችለው ?

10. ለምን ነበር ሁሉም ወደ አቶ ሙሊንጋ አቅጣጫ የተመለከቱት?

11. ስለ ወደፊት ህይወታቸው አቶ ሙሊንጋ ምን ነገሯቸው?

12. ወደፊት ሊገጥሟቸው ስለሚችሉ ችግሮች መንስኤ አቶ ሙለንጋ ምን ነገሯቸው?

13. እርግጠኛ መሆን የሚገባቸው ምን ላይ እንደሆነ ነገሯቸው ?

14. አቶ ሙሊንጋ የቺሽምባን ቤተሰቦች ለመግለጽ የተጠቀሙባቸው ቃላት ምን ነበሩ?

15. ልቦናቸው ለአቶ ሙሊንጋ የነገራቸው ምን ነበር?

## ተግባር 3

አስጠኛችሁ የጥናት ቡድኑን ለሁለት ትከፍለዋለች/ይከፍላችዋል፡፡ እያንዳንዳችሁ ተራ በተራ ታሪኩን ለቡድናችሁ ጥሩ አድርጋችሁ አንብቡ፡፡

1. በጠረጴዛ ዙሪያ የሚካሄደው ንግግር “ከአንድ ርዕስ ወደ ሌላ ርዕስ ይዘል ነበር”፡፡ ይህ ማለት
   ሀ. አንድ ወይም ሁለት ርዕሶች ላይ ብቻ ተነጋግረዋል ማለት ነው፡፡
   ለ. እያንዳንዱ ሰው አንድ ርዕስ ላይ ብቻ በየተራ ተናግረዋል ማለት ነው፡፡
   ሐ. በርካታ ርዕሶች ላይ በፍጥነት ተነጋግረዋል ማለት ነው፡፡

2. “ፍትህ አልበኝነትን ማስወገድ” ማለት

ሀ. የምትፈልጉትን ነገር ለማግኘት ፍትህ አልባ የሆኑ ድርጊቶች መፈጸም

ለ. ፍትህ አልባነትን ማስቆም

ሐ. ፍትህ አልባነት እንዲቀጥል ማድረግ

3. “ምን አለ በለኝ” ማለት

ሀ. ልታምነኝ ይገባል

ለ. የተናገርኩትን ለሁሉም ሰው አዳርስ

ሐ. የተናገርኩት ቀልዴን መሆኑን እንድታውቅ

## ተግባር 4

ከታች የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን እንድትሰሩ አስጠኚያችሁ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| አንድነት | ምክንያት | ትዕግስት | ማጣት | ተደነቀች | የተጠበቀው |
| ሃላፊነት | የሚሰማው | ጡረታ | መንስኤ | ጥረት | ታማኝ |

## ተግባር 5

ከላይ የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች አሟሉ፡፡

1. ቤተሰቡ ውስጥ ________________________________ ስላለ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ሌላውን ከመርዳት ወደኋላ አይልም፡፡
2. ______________________________ አላስፈላጊ መሆኑን ስለምታውቅ በጥሞና ጠበቀች፡፡
3. _________________የሚሰማው ስለሆነ ስራውን በተገቢው መንገድ መስራቱን አረጋገጠ፡፡
4. ወደ ስራ ዘግይተህ ለመጣህበት በቂ _______________________ እንዳለህ እርግጠኛ ነኝ፡፡
5. ጥሩ ምርት ለማግኘት ብዙ __________________________________________ ይጠይቃል፡፡
6. _________________________________ ከወጣ በኋላ ሱቅ መስራቱን አቁሞ ጊዜውን ሙሉ በሙሉ በእርሻ ስራ ላይ አዋለ፡፡
7. እናታቸው ቤት ስትመለስ እራት ተዘጋጅቶ ማግኘቷ ያልጠበቀችው ስለነበረ _______________________________፡፡
8. አውቶቡሱ ይደርሳል ተብሎ__________________________ ጠዋት በ2 ሰዓት ሲሆን ነገር ግን አንድ ሰዓት ዘግይቶ ደረሰ፡፡
9. እርሱ __________________________ በመሆኑ የሰራውን ጥፋት ለጓደኛው በግልጽ ነገረው፡፡

10. ለወንዙ መሙላት______________________________ የሆነው ሀይለኛ ዝናብ መዝነቡ ነው፡፡

## ተግባር 6

አስቸጋሪ የሆነባችሁን ነገሮችን ለማከናወን በርካታ ጥረቶችን አድርጋችሁ የተሳካላችሁን ጊዜ የሚገልጹ ጥቂት አረፍተ ነገሮችን ፃፉ፡፡

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

# ትምህርት 7

# የእግር ኳስ ግጥሚያ

**አስጠኛችሁ ታሪኩን ስታነብላችሁ/ሲያነብላችሁ በደምብ ተከታተሉ፡፡**
**አዲስ ወይም አስቸጋሪ ሆነው ያገኛችሁትን ቃል ከስሩ አስምሩበት፡፡**

---



በሚቀጥለው ቀን ከቡሚ ሶስት ኪሎ ሜትር ላይ በምትገኘው ጎረቤት መንደር መካከል የሚደረግ የእግር ኳስ ግጥሚያ ነበር፡፡ ጎዲዊንና ቺሽምባ ቡሚን በሚወክለው የእግር ኳስ ቡድን ውስጥ አባል ናቸው፡፡ የእነ ሙሶንዳ ቤተሰብ በሙሉ ጨዋታውን ለመመልከት እንደሚሄዱ ወሰኑ፡፡ የሮዝ አያቶች የሚኖሩት በዚሁ አጎራባች መንደር ውስጥ ስለሆነ ቤተሰቡ ጠዋት ከእነሰ-ጋር በማሳለፍ ከሰዓት በኋላ ወደ ጨዋታው ስፍራ ይሄዳሉ፡፡ ማለዳም ተነስተው በእግራቸው ጉዞ ጀመሩ፡፡

የሙሶንዳ አያቶች ቤት እንደደረሱ ጎዲዊንና ቺሽምባ ለጨዋታው ዝግጅት ለማድረግ ተጣድፈው ወጥተው ሄዱ፡፡ሮዝ ና ሙሶንዳ አያቶቻቸውን ጥቂት ስራዎች አገዙ፡፡ እንደጨረሱ ከሙሶንዳ ታናሽ ወንድም ጋር በመሆን መንደሩ ውስጥ እየዞሩ ጥቂት ልጆችን አሰባሰቡ፡፡ አያታቸው ቤት በማምጣት አስተማሯቸው፡፡ ሮዝ መዝሙሮችንና ውብ የሆነ አንድ ጥቅስ አስተማረቻቸው፡፡ ትምህርቱን እንደጨረሱ ሴት አያታቸው የበሶ ጭብጦ ሰጧቸው ልጆቹም ከበሉ በኋላ በሩጫ ወደ ቤታቸው ሄዱ፡፡ ከዚያም የምሳ ሰዓት ደረሰ፡፡

የሙሶንዳ እናትና ሴት አያት ግሩም የሆነ ምግብ አዘጋጅተዋል፥ ቀስ በቀስ እያንዳንዳቸው በገበታው ዙሪያ ተሰባሰቡ፡፡ ወንድ አያቷና አባቷ ከእርሻ ቦታ መጡ፥ጎዲዊንና ቺሽምባ ከልምምድ ተመልሰዋል፡፡ ቤተሰቡ በሙሉ ስለሚካሄደው ጨዋታ ተደስቷል፡፡ “ብዙ አትብሉ፥ በኋላ በደምብ መጫወት ስላለባችሁ” በማለት ለወንዶቹ ልጆች ነገሯቸው፡፡

ጨዋታው የተጀመረው የከሰዓት በኋላው አጋማሽ ላይ ነበር፡፡ የቡሚ ቡድን የመጀመሪያዋን ግብ አስቆጠረ፥ ቀሪውንም የጨዋታ ጊዜ የሚመራው ይህ ቡድን ነበር፡፡ ነገር ግን ጨዋታው ሊጠናቀቅ አስራ አምስት ደቂቃዎች ሲቀሩት ተቃራኒው ቡድን ሁለት ግቦችን አስቆጥሮ አሸናፊ ሆነ፡፡ ቀኑ ከፍተኛ የመፈንደቂያ ሆኖዋል፡፡

ከመጨለሙ አንድ ሰዓት በፊት ቤተሰቡ ወደ ቡሚ ተመለሰ፡፡ ብዙ ርቀው ሳይጓዙ ነበር ከፊታቸው በርቀት አንዲት ሴት ለማገዶ የሚሆን እንጨት በጀርባዋ ተሸክማ ስትሄድ የተመለከቱት፡፡ እየቀረቧት ሲመጡ የተሸከመችው ከባድ በመሆኑ ሊደክማት እንደሚችል ለመገመት ቻሉ፡፡ ጎዲዊንና ቺሽምባ ወዲያውኑ እናግዝሽ ብለው የተሸከመችውን ሲቀበሏት

አመሰገነቻቸው፡፡ የማገዶውን እንጨት እቤቷ ድረስ ሊያደርሱ ሲሄዱ የተቀሩት የቤተሰብ አባላት ወደ ቡሚ ጉዟቸውን ቀጠሉ፡፡

ጎዲዊንና ቺሽምባ ሴትየዋን ከረዱ በኋላ ጉዛቸውን ወደ ቡሚ አቀኑ፡፡በቂ ጉልበት ስለነበራቸው ከሁሉም ቀድመው ቤታቸው ለመድረስ ወሰኑ፡፡ "በእርሻ ውስጥ አቋራጭ መንገድ አውቃለሁ፥ ተከተለኝ ብቻ" አለ ቺሽምባ፡፡ መንገዱን ተያያዙት፡፡ የተቀረው የቤተሰብ አባላት ቤታቸው ሲደርሱ ጎዲዊንና ቺሽምባ በር ላይ ቆመው አገኟቸው፡፡ ደክሟቸዋል፥ሆኖም ግን እየሳቁ ነበር፡፡

## ተግባር 1

አስጠኛችሁ የጥናት ቡድኑን በጥንድ በጥንድ ትከፍላችኋለች/ይከፍላችኋል፡፡ በየተራ አንዳችሁ ለሌላችሁ ጥሩ አድርጋችሁ አንብቡ፡፡

## ተግባር 2

አስጠኛችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡ ጥያቄዎቹ ላይ ከተወያያችሁ በኋላ መልሱን በግላችሁ ፃፉ፡፡

1. የእግር ኳስ ጨዋታ የተካሄደው የት ነበር?

______________________________

2. በአጎራባች መንደር ውስጥ የሚኖሩት እነማን ነበሩ?

______________________________

3. የቤት ውስጥ ስራ ከሰሩ በኋላ ሮዝና ሙሶንዳ ምን አደረጉ?

______________________________

4. ሮዝ ልጆቹን ምን አስተማረች?

______________________________

5. ልጆቹ ቤታቸው ከመመለሳችው በፊት ሴት አያታቸው ምን ሰጠቻቸው?

______________________________

6. ቤተሰቡ ምሳቸውን የት ተመገቡ?

______________________________

7. እነዚህ ሰዎች ከምሳ በፊት ምን እያደረጉ ነበር?

- ጎዲዊንና ቺሽምባ ________________________________
- ሮዝና ሙሶንዳ ________________________________
- የሙሶንዳ እናትና ሴት አያት ________________________________
- የሙሶንዳ አባትና ወንድ አያት ________________________________

8. ወንዶቹ ልጆች ብዙ እንዳይበሉ የተነገራቸው ለምንድን ነው ?

________________________________

9. የኳስ ግጥሚያውን ያሸነፈው የትኛው ቡድን ነው?

________________________________

10. ቤተሰቡ ወደ ቡሚ ሲመለስ ስንት ሰዓት ነበር?

________________________________

11. በመንገድ ላይ ማንን አገኙ?

________________________________

12. ቺሽምባ እና ጎዲዊን ምን አደረጉ?

________________________________

13. ቤት ቀድሞ የደረሰው ማን ነበር፥ ቤተሰቡ ወይስ ወንዶቹ ልጆች? ለምን?

________________________________

## ተግባር 3

አሁን ደግሞ አስጠኛችሁ መልመጃዎችን ታነብላችሁ/ያነብላችሁና ትክክለኛውን መልስ እንድታከቡ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡

1. ቤተሰቡ ወደ አጎራባች መንደር “ በእግራቸው ተጓዙ ” ይህ ማለት

   ሀ. ወደ መንደሩ ተራመዱ

   ለ. ወደ መንደሩ በፈረስ ተጓዙ

   ሐ. አውቶቡስ መናኸሪያ ድረስ በእግራቸው ከሄዱ በኋላ በአውቶቡስ ተሳፍረው ወደ መንደሩ ሄዱ፡፡

2. ጎዲዊንና ቺሽምባ “በቂ ጉልበት” አላቸው፡፡ ይህ ማለት

   ሀ. ብዙ ተመግበዋል

ለ. ለረጅም ሰዓት ፀሐይ መቷቸዋል

ሐ. አልደከማቸውም፥ ስለሆነም አንድ ነገር ለማድረግ ዝግጁ ናቸው ::

## ተግባር 4

ከታች የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን እንድትሰሩ አስጠኚያችሁ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል::

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ተሸከመላቸው | ለገሰ | አዘጋጁ | ታየች | አጎራባች |
| ልምምድ | የቤት ስራቸውን | ቀጠሉ | ፈጥነው | ጉልበቱን |

## ተግባር 5

ከላይ የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች አሟሉ::

1. የሙሶንዳ አያቶች የሚኖሩት ______________________ ማህበረሰብ ውስጥ ነው::
2. ልጆቹ በማለዳ ተነስተው የተለመደውን ______________________ ያጠናቅቃሉ::
3. ልጃገረዶቹ እራት የሚበላበትን ገበታ ______________________ ::
4. በአንድ ነገር ጥሩ ደረጃ ላይ ለመድረስ በርካታ ______________________ ማድረግ አስፈላጊ ነው::
5. ለእንስሳቱ መኖሪያ የሚሆን ቤት ለመስራት እርዳታውን ______________________ ::
6. እግሩ ክፉኛ ስለተቆረጠ ጓደኞቹ ______________________ ወደ ጤና ጣቢያ ወሰዱት::
7. ______________________ ስለጨረሰ ከአሁን በኋላ ስራውን ማከናወን አይችልም::
8. በማለዳ ተነስታ ፀሎቶቿን እያደረገች ሳለ ፀሐይ ከአድማሱ ውስጥ በዝግታ በመውጣት ______________________ ::
9. ወጣቱ ልጅ አዛውንቷ ሴት የያዙትን ሻንጣ ______________________ ::
10. ልጆቹ በዝናብ ውስጥ ጨዋታዎቻቸውን መጫወት ______________________ ::

## ተግባር 6

ከቡድን ጓደኞችሁ ጋር በመሆን በዚህ ትምህርት ውስጥ ያለውን ትረካ መሰረት በማድረግ አንድ አጭር ድራማ እንድትሰሩ አስጠኛችሁ ትረዳችኋለች/ይረዳችኋል::

# ትምህርት 8

# ጤና ጣቢያ

**አስጠኛችሁ ታሪኩን ስታነብላችሁ/ሲያነብላችሁ በደምብ ተከታተሉ፡፡**
**አዲስ ወይም አስቸጋሪ ሆነው ያገኛችሁትን ቃል ከስሩ አስምሩበት፡፡**

---

አንዳንድ ጊዜ ሙሶንዳና ሮዝ ወ/ሮ ፊሪ የምትባል ወዳጃቸውን ከሰዓት በኋላ ከስራ ስትመለስ ሊጠይቋት ይሄዳሉ፡፡ ወ/ሮ ፊሪ በጤና ጣቢያ ውስጥ የምትሰራ ነርስ ነች፡፡ አንድ ቀን ልጃገረዶቹወደ ጤና ጣቢያ በመሄድ እገዛ ማድረግ ስለፈለጉ ጥያቄ አቀረቡላት፡፡ "እንዴት ያለ ጥሩ ሀሳብነው!" አለች ሲስተር ፊሪ፡፡



"ሰኞ ዕለት ኑ፥ እናቶች እድሜያቸው ከአምስት አመት በታች የሆኑትን ህፃናት ለማስመርመር በጠዋት ይመጣሉ፡፡ ምርመራው እንዳለቀ ስለ አመ ጋገብ ዘዴ ለእናቶች ተጨማሪ ትምህርት ይሰጣል፡፡"ትምህርቱ እየተሰጠ ልጆቻቸውን ስለሚጠብቁ ለመከታተል አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል፡፡ለሙሶንዳ ታናሽ ወንድምና እህቶች እንዴት ጥሩ እንደሆነችላችሁ ተመልክቻለሁ፥ ምናልባትም ለእናቶቻቸው ትምህርት ሲሰጥ እናንተ ልጆቹን ልታስተምሩ ትችላላችሁ፡፡" በሚቀጥለው ቀን ሁለቱ ልጃገረዶች ከሲስተር ፊሪ ጋር በመሆን ወደ ጤና ጣቢያ ሄዱ፡፡

ወላጆቹ የሚማሩበት ሰዓት ሲደርስ ሙሶንዳና ሮዝ ልጆቹን ወደ ውጭ በመውሰድ ዛፍ ጥላ ስር ይዘዋቸው ተቀመጡ፡፡ አብረው መዝሙር ዘመሩ፥ ጨዋታዎችን ተጫወቱ፡፡ ሮዝ አንድ ታሪክ ነገረቻቸው፡፡ ልክ ታሪኩ እንዳበቃ እናቶቻቸው ልጆቻቸውን ለመሰብሰብ መጡ፡፡ ሁሉም ደስተኞች ነበሩ፡፡ ሲስተር ፊሪ ና ሌሎች የጤና ጣቢያው ሰራተኞች በጣም ተደሰቱ፥ በሚቀጥለው ቀን እንዲመጡ ልጃገረዶቹን ጠየቋቸው፡፡

ወደ ቤታቸው በመሄድ ላይ ሳሉ ሙሶንዳ በጣም ታስብ ነበር፡፡ በስተመጨረሻም ዝምታውን ከሰበረች በኋላ ለሮዝ እንዲህ አለቻት፥ "በዛሬው ዕለት ከህፃናት ጋር የሆነውን ነገር ከማረጋገጫ ጋር ግንኙነት ሊኖረው ይችላል ብለሽ አታስቢም?" አንቺ አስተማሪ ብትሆኚ ትወጃለሽ እኔ ደግሞ ነርስ፥ይሄውና በጤና ጣቢያ ውስጥ ሆነን ህፃናትን እያስተማርንና እየተንከባከብን ነን፡፡"

**ተግባር** 1

አስጠኛችሁ የጥናት ቡድኑን በጥንድ በጥንድ ትከፍላችኋለች/ይከፍላችኋል፡፡ በየተራ አንዳችሁ ለሌላችሁ ጥሩ አድርጋችሁ አንብቡ፡፡

## ተግባር 2

አስጠኛችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡ ጥያቄዎቹ ላይ ከተወያያችሁ በኋላ መልሱን በግላችሁ ፃፉ፡፡

1. አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ ሙሶንዳና ሮዝ ማንን ለመጎብኘት ሄዱ?

______________________________

2. ሲስተር ፊሪ የምትሰራው የት ነው?

______________________________

3. ልጃገረዶቹ ሲስተር ፊሪን ምን ጠየቋት?

______________________________

4. ዘወትር ሰኞ ዕለት በጤና ጣቢያ ውስጥ ምን ይከናወናል?

______________________________

5. ልጃገረዶቹ በጤና ጣቢያ ውስጥ ምን ሊሰሩ ይችላሉ ብላ ሲስተር ፊሪ አሰበች?

______________________________

6. እናቶቻቸው ትምህርት እየተከታተሉ ሳለ ከህፃናት ልጆቻቸው ጋር ሮዝና ሙሶንዳ ምን አደረጉ?

______________________________

7. ወደ ቤታቸው በመመለስ ላይ ሳሉ ሙሶንዳ ስለ ምን አሰበች?

______________________________

## ተግባር 3

አሁን ደግሞ አስጠኛችሁ መልመጃዎችን ታነብላችሁ/ያነብላችሁና ትክክለኛውን መልስ እንድታ ከቡ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡

1. እናቶች “ልጆቻቸውን ለመሰብሰብ” የመጡት ልክ ሮዝ ታሪኩን ስትጨርስ ነው፡፡ ይህ ማለት፣

   ሀ. እናቶቻቸው የመጡት ልጆቻቸውን ወደ ቤት ለመውሰድ ነው፡፡

ለ. እናቶቻቸው መጥተው ልጆቹን አቅፈው ያዟቸው፡፡

ሐ. እናቶቻቸው ከመጡ በኋላ ቆመው ጠበቋቸው፡፡

2. በስተመጨረሻ “ዝምታዋን ሰበረች” የሚለው ሀረግ ምን ማለት ነው?

ሀ. ከዝምታ ቆይታ በኋላ ወደቀች፡፡
ለ. ከዝምታ ቆይታ በኋላ መናገር ጀመረች፡፡

ሐ. ከዝምታ ቆይታ በኋላ አንድ ነገር ሰበረች፡፡

## ተግባር 4

ከታች የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን እንድትሰሩ አስጠኚያችሁ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሀሳቢ | ጤና ጣቢያ | ሀሳብ | የጤና | አመጋገብ ዘዴ |
| በሚቀጥለው | ተደሰተች | ልትጎበኘን | ያመጣሉ | ምርመራ |

## ተግባር 5

ከላይ የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች አሟሉ፡፡

1. ነርሷ ስለ ________________________ ንግግር ካደረገች በኋላ ጤናማ የሆኑትን የምግብ ዝርዝር የያዘ ጽሑፍ ለህጻናቱ ወላጆች አደለች፡፡
2. የታመመባትን ልጅ ለነርሷ ለማሳየት ወደ ________________________________ ሄደች፡፡
3. ወደ ቤቷ ስትሄድ ለእናቷ አበባ ቀጥፋ ለመሄድ በማሰቧ ጥሩ ______________________ ነው ብላ እሷ ለራሷ አሰበች፡፡
4. ግጥሙን ካነበበች በኋላ በጣም ________________________________________________ ፡፡
5. ____________________________________ ቀን ብዙ ስራ ስለሚጠብቀው ዛሬ በጊዜ ተኛ፡፡
6. አያቴ የእድሜ ባለጸጋ ብትሆንም እንኳ በአሁኑ ወቅት በጥሩ_______________________ ሁኔታ ላይ ትገኛለች፡፡
7. ታናሽ እህቷን በመንከባከብ ስራ እናቷን ስለረዳች ልጄ ጥሩ ______________________ ሆናለች ብላ ልቧ በደስታ ተሞላ፡፡
8. የአክስቴ ልጅ ________________________________________ ትላንት ቤታችን መጣች፡፡
9 አባቴ ጤና ስለማይሰማው ________________________ ለማድረግ ወደ ሆስፒታል ሄደ፡፡
10. ገበሬዎቹ የፍራፍሬና አትክልት ምርቶቻቸውን ወደ ገበያ ዘወትር ሰኞ ______________________________________________________________________ ፡፡

## ተግባር 6

በዚህ የትምህርት ክፍል ውስጥ ስለተማራችሁት አንድ ወይም ሁለት አረፍተ ነገሮችን ፃፉ፡፡

## ተግባር 7

ሙሶንዳና ሮዝ ለልጆቹ ያስተማሯቸው መዝሙር ይህ ነበር፡፡
አስጠኛችሁ እንዴት እንደምትዘምሩት ታስተምራችኋለች/ያስተምራችኋል፡፡

**<u>ሰዎችን አፍቅሩ</u>**

ፍቅር ፍቅር ፍቅር ፍቅር

ሰዎችን አፍቅር፡፡

ፍቅር ፍቅር ፍቅር ነው
አለም የተጀመረው በእንደዚህ ነው፡፡

እግዚአብሔር ፍጥሮቹን ያፈቅራል
ስላፈቀረን ነው የፈጠረን

አፍቅሩ አፍቅሩ እሱንና ፍጥሩን

የእግዚአብሔርን ፍጡሮች አፍቅሩ
ትልቅም ቢሆኑ ትንሽ፡፡

እያንዳንዱን ሰው እንደ
ሚያበራ ኮከብ ተመልከቱት፡፡

እግዚአብሔር ፍጥሮቹን ያፈቅራል
ፈጥሯቸዋልና

እርሱንና የሰውን ዘር አፍቅሩ ፥ አፍቅሩ፥ አፍቅሩ፡፡

ይህንን መዝሙር ለምታውቋቸው ጥቂት ልጆች ልታስተምሯቸው ትችላላችሁ፡፡

# ትምህርት 9

## ልዩ ስፍራ

**አስጠኛችሁ ታሪኩን ስታነብላችሁ / ሲያነብላችሁ በደምብ ተከታተሉ፡፡ አዲስ ወይም አስቸጋሪ ሆነው ያገኛችሁትን ቃል ከስሩ አስምሩበት፡፡**

---



ሙሶንዳ ብቻዋን መሆንና ስለ ነገሮች ማሰብ በምትፈልግበት ጊዜ ወደ ልዩ ስፍራ ትሄዳለች፡፡ ይህም ስፍራ የሚገኘው ከአንድ ወንዝ አጠገብ ነው፡፡ ከረጅም የማንጎ ዛፍ ጥላ ስር አንድ ጠፍጣፋ ቋጥኝ ድንጋይ አለ፡፡ ሙሶንዳ ቋጥኝ ድንጋዩ ላይ ትወጣለች፡፡ ከዚያም በጀርባዋ ተንጋላ ተኝታ የዛፉን ቅጠሎች፥ ቅርንጫፎችንና በመካከላቸው የሚታየውን ጥርት ያለውን ሰማይ ትመለከታለች፥ የወፎቹን ዝማሬና ወንዙ ሲፈስ የሚያሰማውን ድምጽ ትሰማለች፡፡ በጣም ውብ ስፍራ ነው፡፡ ሙሶንዳ እዚህ ስፍራ ስትሆን ሁል ጊዜ የተረጋጋችና ደስተኛ ትሆናለች፡፡

ሮዝ ከእሷ ጋር ለማሳለፍ በምትቆይባቸው ጥቂት ሳምንታት ሁለቱ ልጃገረዶች ስለ በርካታ ነገሮች ተወያይተዋል፡፡ የሙሶንዳ አእምሮ በብዙ ነገሮች ተሞልቷል፡፡ ለዚህም ነው አንድ ቀን ጠዋት ተነስታ ወደምትወደው ስፍራ የሄደችው፡፡ በቋጥኙ ላይ ጋደም እንዳለች በጤና ጣቢያ ውስጥ ስለአሳለፉት ቀን አሰበች፡፡ “አንድ የሚጠቅም ስራ መስራት እንዴት ጥሩ ነው፡፡” ብላ ለራሷ አሰበች፡፡ አባቷ ዘወትር ስለሚነግሯት አሰበች፥ “ ዛፎች ፍሬ ማፍራት ይገባቸዋል” በመቀጠልም በመደነቅ “የእኔ ህይወት ፍሬ እያፈራ እንደሆነ እንዴት አውቃለሁ?”ወዲያውኑ “ማረጋገጫ” የሚለውን ቃል አሰበች፡፡

ወዲያውኑ በመቀጠል ሀይለኛ ነፋስ ነፈሰ፡፡ ጥቂት ቅጠሎችን ከዛፍ ላይ አረገፋቸው፡፡ከቅጠሎቹ ጋር አንዲት ቢጫ ወፍን ተመለከተች፡፡ ነፋሱ ሲያቆም ቅጠሎቹ ውሀው ላይ ሲረግፉ ወፏ ግን መብረሯን ቀጠለች፡፡ ወፏን ስትመለከት አንድ ሀሳብ በአእምሮዋ ውስጥ መጣላት፡፡ ነፋሱ ለትንሿ ወፍ ሀይል ሰጣት፥ አሁን በከፍታ ስፍራ ላይ እየበረረች ነው፡፡ ምናልባትም ማረጋገጫ የሚባለው ይህ ሊሆን ይችላል፡፡ ወፏ ለመብረር ጥረት ስላደረገች፥ ነፋሱ ጥረቷን አገዛት፡፡

ከቋጥኙ ወርዳ ወደ ቤቷ ተመልሳ ያየቻቸውንና ያሰበችውን ሁሉ ለሮዝ ለመንገር ሄደች፡፡ ነፋሻው አየር ፊቷ ላይ ሲያርፍ የደስታ ስሜት ተሰማት፡፡

**ተግባር** 1

**አስጠኛችሁ የጥናት ቡድኑን በጥንድ በጥንድ ትከፍላችኋለች/ይከፍላችኋል፡፡ በየተራ አንዳችሁ ለሌላችሁ ጥሩ አድርጋችሁ አንብቡ፡፡**

**ተግባር** 2

**አስጠኛችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡ ጥያቄዎቹ ላይ ከተወያያችሁ በኋላ መልሱን በግላችሁ ፃፉ፡፡**

1. **ሙሰንዳ የምትወደው ልዩ ስፍራ የሄደችው ምን ጊዜ ነበር**?

___

2. **ከማን ጋር ሄደች**?

___

3. **የምትወደው ልዩ ስፍራ የት ነው የሚገኘው** ?

___

4. **ሙሰንዳ በዚህ ስፍራ በነበረችበት ጊዜ ምን ተሰማት**?

___

5. **በዚህ ጊዜ ወደ ልዩ ስፍራዋ ለመሄድ ለምን ወሰነች**?

___

6. **እዚያ በነበረችበት ጊዜ ስለ ምን አሰበች**?

___

7. **የሙሰንዳ አባት ዘወትር የሚሉት ምን ነበር**?

___

8. **ከቅጠሎቹ ጋር ተቀላቅሎ በነፋስ ሲወርድ ሙሰንዳ ያየችው ምን ነበር**?

___

9. **ነፋሱ ሲያቆም ቅጠሎቹ ምን ሆኑ**?

___

10. **ትንሿ ቢጫ ወፍ ምን ሆነች**?

___

11. ወፏ በነፋሱ ታግዛ ወደ ከፍታ ስትበር ስትመለከት በሙሶንዳ አእምሮ ውስጥ ምን ሀሳብ ተከሰተላት?

---

## ተግባር 3

አሁን ደግሞ አስጠኛችሁ መልመጃዎችን ታነብላችሁ/ያነብላችሁና ትክክለኛውን መልስ እንድታከቡ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡

1. የሙሶንዳ አእምሮ "በሀሳብ ተሞልቷል" ይህ ማለት

   ሀ. ብዙ ጥያቄዎች አሏት፡፡

   ለ. በርካታ ስለሆኑ ነገሮች ታስባለች፡፡

   ሐ. ለማሰብ በጣም ደክሟታል፡፡

2. ህይወቷ "መልካም ፍሬዎችን እንደሚያፈራ" ሙሶንዳ ተስፋ አድርጋለች፡፡ ይህ ማለት

   ሀ. በህይወቷ ውስጥ ጥሩ ነገሮችን ለማከናወን ተስፋ አድርጋለች፡፡

   ለ. ተርባለች

   ሐ. እያደገች ስትመጣ የእርሻ መሬት እንደሚኖራት ተስፋ አድርጋለች፡፡

3. ሙሶነዳ ወፎቹን እየተመለከተች " አንድ ሀሳብ በአእምሮዋ ውስጥ መጣላት"፡፡ ይህ ማለት

   ሀ. አንድ ጥያቄ አላት

   ለ. አንድ ሀሳብ አላት

   ሐ. ወፏ ወዴት እንደበረረች ተደነቀች

## ተግባር 4

ከታች የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን እንድትሰሩ አስጠኚያችሁ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ጥላ | መፍሰስ | የምትወደው | ጠፍጣፋ | ማስታወስ |
| መወሰን | ተመለከተ | ማለት | ነፋሻ | ጠቀሜታ |

## ተግባር 5

ከላይ የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች አሟሉ፡፡

1. ቀኑ በጣም ሞቃት ስለነበር ምሳችንን በዛፍ ______________________ ስር ሆነን በላን፡፡
2. ቤት ለመስሪያ የሚሆን _________________________________ መሬት እየፈለገ ነው፡፡
3. ዘወትር ጠዋት የምታደርገው አንድ _____________________________ ፀሎት አላት፡፡
4. በበሬ የሚጎተት ጋሪ ከባድ ነገሮችን ለማጓጓዝ _________________________ ይሰጣል፡፡
5. ቀዝቃዛና ___________________________ አየር ክፍት በሆነው መስኮት ወደ ቤት ገባ፡፡
6. ለወንዙ በፍጥነት __________________________ ምክንያት ከባድ ዝናብ መዝነቡ ነው፡፡
7. የመዝሙሩን ግጥም ___________________________________________ አልቻለችም፡፡
8. ታላቅ ወንድሙ ጫማውን ሲያስርለት ታናሽየው እንዴት እንደሚያስር _________________________________________ ፡፡
9. የልጃቸውን ስም ለማውጣት አስበው ማን ብለው እንደሚጠሩት መምረጥና _______________________________ አቃታቸው፡፡
10. አንድ ማንጎ ውስጡ ቢጫ ሆነ __________________ለመበላት ዝግጁ ሆኗል ማለትነው፡፡

## ተግባር 6

ከታች የተሰጠውን ባዶ ቦታ ከሞላችሁ በኋላ ጥቅሱን በቃላችሁ ያዙ

> **“ አላማቸው የሰውን ዘር ለማገልገል÷ ጥረቶቻቸውና ልፋታቸው ለሁሉም የሰው ዘር መልካምነትና መሻሻል ብለው ራሳቸውን ላተጉ ነፍሶች እግዚአብሔር እረዳታቸው ነው፡፡”**

____________ የሰውን ዘር ____________ ÷ ______________ ______________________

ለሁሉም የሰው ዘር ________________ _____________________ ብለው ራሳቸውን ላተጉ

ነፍሶች እግዚአብሄር ____________________________________ ነው፡፡


# ትምህርት 10

# ብስክሌት መጠገን

አስጠኛችሁ ታሪኩን ስታነብላችሁ/ሲያነብላችሁ በደምብ ተከታተሉ፡፡
አዲስ ወይም አስቸጋሪ ሆነው ያገኛችሁትን ቃል ከስሩ አስምሩበት፡፡

---

አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ ሙሶንዳ ውሃ ቀድታ ወደ ቤት ስትመለስ ጎዲዊን የቺሽምባን ብስክሌት እየጠገነ ደረሰች፡፡ ከአጠገቡ በሚገኝ ጥላ ስር ተቀምጣ ሲጠግን ተመለከተችው፡፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ እንዲህ ስትል ጠየቀችው፥ "ልጆች ሆነን እንዴት ስንጫወት እንደነበረ ታስታውሳለህ?"



"በጫካ ውስጥ እንዳለ አዳኝ እያስመሰልን የዱር አውሬ ስንፈልግ " በማለት መለሰላት፡፡

"እንኮኮ አድርገሽኝ መንገድ እየመራሁህ ስንሄድ እንኳን" አለች ሙሶንዳ እሱ ባለው ላይ በማከል፡፡ "ነገሮች ሁሉ ተለውጠዋል፥ እኛም እየተለወጥን ነው፡፡"

"አዎን አሁን በጣም ከባድ ስለሆንሽ እንኮኮ ለማድረግ አልችልሽም፡፡" አለና ጎዲዊን ሁለቱም ከት ብለው ሳቁ፡፡

"ስለ ወደፊቱ ህይወትህ ታስባለህ፥ ጎዲዊን?" ሙሶንዳ ጠየቀችው፡፡ "ምን ለመሆን ትፈልጋለህ?"

ጎዲዊን ብስክሌቱን መስራቱን ቀጠለ፥ "አላውቀውም፡፡ ገንዘብ ማግኘት ግን እፈልጋለሁ፥ቤተሰቦቻችንን መርዳትና አንድ ቀን እኔም ቤተሰብ መስርቼ መኖር እፈልጋለሁ፤" በማለት መለሰ፡፡

"ስለ ተሰጥዖዎችህ አስበህ እንዴት መጠቀም እንዳለብህ አስበህበት ታውቃለህ?"በማለት ሙሶንዳ ጠየቀችው፥ "እኔና ሮዝ ስለዚህ ብዙ ተነጋግረንበታል፡፡"

"አውቃለሁ፥ አውቃለሁ" አለ የቡሉን መፍቻውን እያነሳ፡፡ "እናንተ ሁልጊዜ የምታወሩት ስለ ማረጋገጫ ነው... ጥረት በምናደርግበት ጊዜ እግዚአብሔር ስለሚረዳን፡፡"
"ታዲያ ይህ እኮ እውነት ነው፥ ጎዲዊን " አለችና ቀጥላ ስለ ቢጫዋ ወፍ ታሪክና ስለ ነፋሱ

ነገረችው፡፡

ወዲያውኑ ቺሽምባ መጣ "ሰላም ብያለሁ" አለና "ብስክሊቷ እንዴት ነች? ችግሯን ማግኘት ችለሀል?" በማለት ጠየቀው፡፡

"ችግሩ ያለው ጥርሶቹ ላይ ነው፥ እያስተካከልኩት ነው፡፡" በማለት ብሎኑን እያጠበቀ መለሰለት፡፡

"እንደምታስተካክለው ጥርጥር የለኝም!" አለ በመቀጠልም ሙሶንዳን እየተመለከታት "ወንድምሽ መካኒክ እንደሆነ ታውቂ ነበር?"

ሮዝ ንግግራቸውን በከፊል ስለሰማች ከቤት ወጥታ መጣችና "ጎዲዊን! ይህ ካንተ ተሰጦዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ነገሮችን በመጠገን የተካንክ ነህ፥ ጥሩ መካኒክ መሆን ትችላለህ!"

"አንድ ብስክሊት መጠገን በመቻሌ ?" አለ ጎዲዊን "ይህ መካኒክ ሊያስብለኝ አይችልም፡፡ ስልጠና ያስፈልገኛል፡፡"

የተቀሩት ሶስቱም ሳቁና እንዲህ አሉ " ስለዚህ ጥረት አድርግ! " ሁሉም ሳቁ፥ ጎዲዊን አብሯቸው ሳቀ፡፡

"ጎዲዊን፥ ለምን አቶ ቺዬሱን አታናግራቸውም፡፡ እዚያ ገበያው አጠገብ ጋራዥ ያላቸው እንኳ ን? ምናልባት ሊያሰለጥኑህ ይችላሉ፡፡" አለ ቺሽምባ ደስታ በተሞላበት አነጋገር፡፡

"አዎን ያ የመጀመሪያ ጥረትህ ሊሆን ይችላል፡፡" አለች ሮዝ በማከል፡፡

"ምን ማለታችሁ ነው? በማለት ጎዲዊን  ጠየቀ፡፡ " እኔኮ ሂጄ እንደዚህ አድርጉልኝ ብዬ መጠየቅ አልችልበትም፥ ደግሞም አልግባባቸውም፡፡"

"እኔ እግባባቸዋለሁ፥ስለዚህም ላስተዋውቅህ እችላለሁ፡፡ ከፈለክም ነገ አብረን ልንሄድ እንችላለን" አለ ቺሽምባ፡፡

በኋላ ብቻቸውን ሲሆኑ ሮዝ ሙሶንዳን እንዲህ አለቻት "ነገ ጎዲዊን ስለ ማረጋገጫ ምንነት ይረዳል፥" ተሳሳቁና ለወንዶቹ ልጆች ምንም ነገር ላለመናገር ወሰኑ፡፡

**ተግባር** 1

**አስጠኛችሁ የጥናት ቡድኑን በጥንድ በጥንድ ትከፍላችኋለች/ይከፍላችኋል፡፡ በየተራ አንዳችሁ ለሌላችሁ ጥሩ አድርጋችሁ አንብቡ፡፡**

**ተግባር** 2

**አስጠኛችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡ጥያቄዎቹ ላይ ከተወያያ ችሁ በኋላ መልሱን በግላችሁ ፃፉ፡፡**

1. **ሙሶንዳ ውሃ ቀድታ ቤት ስትመለስ ጎዲዊን ምን እያደረገ ደረሰች** ?

___________________________________________

2. **ጎዲዊንና ሙሶንዳ ልጆች ሳሉ የሚጫወቱት ጨዋታ ምን ነበር**?

___________________________________________

3. **ጎዲዊን ወደፊት ምን ለመስራት ይፈልጋል**?

___________________________________________

4. **ሙሶንዳና ጎዲዊን እያወሩ ሳለ የመጣው ሰው ማን ነበር**?

___________________________________________

5. **የቺሽምባ ብስክሊት ችግር ምን ነበር**?

___________________________________________

6. **ከጎዲዊን ተሰጥዖዎች ውስጥ አንዱ ምንድን ነው**?

___________________________________________

7. **ጎዲዊን ምን ሊሆን ይችላል ብላ ሮዝ አሰበች**?

___________________________________________

8. **ጎዲዊን መካኒክ ለመሆን ምን ማድረግ ያስፈልገዋል**?

___________________________________________

9. **ቺሽምባ ለጎዲዊን ያቀረበለት ሀሳብ ምን ነበር**?

___________________________________________

10. ቺሽምባና ጎዲዊን በሚቀጥለው ቀን ምን ለማድረግ ተስማሙ?

_______________________________________________

11. በሚቀጥለው ቀን ምን ሊከሰት ይችላል ብለው ሮዝና ሙሶንዳ አሰቡ?

_______________________________________________

## ተግባር 3

አሁን ደግሞ አስጠኛችሁ መልመጃዎችን ታነብላችሁ/ያነብላችሁና ትክክለኛውን መልስ እንድታከቡ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡

1. " ነገሮች ሁሉ ተለውጠዋል" ስትል ሙሶንዳ ለጎዲዊን ነገረችው፡፡ ይህ ማለት

    ሀ. በፊት ከነበረበት ወደኋላ ቀርቷል፡፡

    ለ. ነገሮች በፊት እንደነበሩት አይነት አይደሉም፡፡

    ሐ. የሚኖሩት የተለያየ አካባቢ ነው፡፡

2. " ችግርን ፈልጎ ማግኘት" ማለት

    ሀ. ችግሩን በስዕል ማስቀመጥ

    ለ. ስለችግሩ ማሰብ

    ሐ. የችግሩን ምክንያት ማግኘት

3. ሮዝ ጎዲዊን ነገሮችን በመጠገን " የተካንክ ነክ " አለችው፡፡ ይህ ማለት

    ሀ. ጎዲዊን ነገሮችን በደምብ መጠገን ይችላል፡፡

    ለ. ጎዲዊን ነገሮችን በመጠገን ከሌሎች ይበልጣል፡፡

    ሐ. ጎዲዊን ነገሮችን ሲጠግን ደስተኛ ነው፡፡

## ተግባር 4

ከታች የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን እንድትሰሩ አስጠኚያችሁ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ለማስመሰል | ስልጠና | ተዋወቃት | መረዳት | መጠገን |
| ሰበሰበች | አጠበቀ | ከባድ | ስለተደሰተች | ተለዋዋጭ |

## ተግባር 5

ከላይ የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች አሟሉ::

1. ልጁ የአባቱን ጫማ አድርጎ በቤቱ ዙሪያ ይንጎማለላል፥ ልጁ የፈለገው እራሱን እንደ ትልቅ ሰው ______________________ ነው::

2. ልጅቷ ትምህርት ቤት ከመሄዷ በፊት ዶሮዎቹ የጣሉትን እንቁላሎች ______________________ ::

3. ልጅቷ በጣም ______________ ስለሆነች እናቷ ልታቅፋት ስላልቻለች አባትየው ታቀፋት::

4. አንድ ልጅ በእድሜዋ ______________________ ከሚገባት በላይ ትረዳለች::

5. ፈገግ ብሎ ሰላምታ ከሰጣት በኋላ ______________________ ::

6. ልጁ የለበሰው ሱሪ ሰፊ ስለነበረ ቀበቶውን በደምብ ______________________ ::

7. የዳቦ መጋገሪያ ምድጃ እንዴት እንደሚሰራ ______________________ ለመውሰድ ወደ ቀበሌ ጽ/ቤት ሄደች::

8. በአሁኑ ወቅት አየሩ በየጊዜው ______________________ ነው::

9. ወንበሩ በርካታ ቦታዎች ላይ ስለተሰባበረ ______________________ አስቸጋሪ ነው::

10. እጅግ በጣም ______________________ ከወንበሯ ዘላ ተነሳች::

## ተግባር 6

ከታች የተሰጡትን ጥያቄዎች ከጓደኛችሁ ጋር በመሆን ከተወያያችሁ በኋላ ጥቅሱን በማጥናት በቃል ያዙት::

**“ በአገልግሎት መንፈስ የሚከናወን ስራ የአምልኮ ከፍተኛ ደረጃ ነው:: ”**

1. የአምልኮ ከፍተኛ ደረጃ የሆነው ምንድን ነው?

______________________________________________

2. የሚከተሉት ባለሙያዎች ለሰው ልጅ የሚሰጡት ግልጋሎት ምንድን ነው? ገበሬ፥ ሀኪም፥ አስተማሪ፥ እናት ፥ ሳይንቲስት፥ አናጢ?

# ትምህርት 11

# መካኒኩ ጎዲዊን

**አስጠኞቻችሁ ታሪኩን ስታነብላችሁ/ሲያነብላችሁ በደምብ ተከታተሉ፡፡**
**አዲስ ወይም አስቸጋሪ ሆነው ያገኛችሁትን ቃል ከስሩ አስምሩበት፡፡**

---

በሚቀጥለው ቀን በጠዋት ተነስተው ቺሽምባና ጎዲዊን ገበያው ወደሚገኝበት ስፍራ ተጓዙ፡፡ ገበያው አጠገብ በመቃረብ ላይ ሳሉ በሚሸጡና በሚገዙ ሰዎች መካከል የሚደረገውን ጫጫታ፥ የዶሮ ጩኸትና በአንዳንድ ሱቆች ውስጥ ከሬዲዮ የሚወጣ ሙዚቃ ይሰማቸው ነበር፡፡



አቶ ቺዬሱ አጭርና ሽምገል ያሉ ሰው ሲሆኑ፣ ከገራዡ ፊት ለፊት ሆነው አንድ ትንሽ ሞተር እያፀዱ ያንጎራጉራሉ፡፡ ቺሽምባን ሲመለከቱ ፊታቸው በደስታ ፈካ፡፡ እናም ተጨባበጡ፡፡

ቺሽምባም ጎዲዊንን አስተዋወቀውና ጥሩ ጠጋኝ እንደሆነ ገለፀላቸው፡፡ ጎዲዊን ደንግጦ ነበር፡፡ ሆኖም ግን እንደምንም ብሎ ለመናገር ሀይሉን በማሰባሰብ ድፍረትን አገኘ፡፡ጎሮሮውን አፀዳና እንዲህ ሲል ተናገረ “ አቶ ቺዬሱ፥ መካኒክ ለመሆን ፍላጎቱ አለኝ፡፡ስለዚህም፥ሳስብ የነበረው ምናልባት እርስዎን በመርዳት መማር ብችል በማለት ነው፡፡”



“ደህና፥ እርዳታህን ለመጠቀም እችላለሁ፥” በማለት አቶ ቺዬሱ መለሱለት፡፡ “ነገር ግን የምከፍልህ ገንዘብ አይኖርም፡፡”

“ግድ የለም፥ መማር ነው የምፈልገው” አለ ጎዲዊን፡፡ “ዛሬ ጠዋቱን በሙሉ እዚህ መቆየት ትችላለህ? ይህ ሞተር ዘይት መጠጣት ያስፈልገዋል፥ ከዚያም በኋላ ተመልሶ መገጣጠም ይኖርበታል፡፡”

“ አሁን? አሁን መጀመር እችላለሁ?” በማለት ጎዲዊን ጠየቀ፥ በመደነቅ፡፡
“ እንዴታ!” አሉና ሳቁ አቶ ቺዬሱ፡፡ “እጅህን ወደ ላይ ጠቅልልና ወደ ስራህ ተሰማራ!”

ጎዲዊን አዲሱን ስራ በጉጉት ጀመረ፡፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ቺሽምባ ለመሄድ ተነሳና አቶ ቺዬሱን ደህናዋሉ በማለት ተሰናበተ፡፡ ወደ ጎዲዊን ተጠግቶ “ማረጋገጫ” በማለት በጆሮው ነገረው፡፡

ወደ ቤቱ በመመለስ ላይ ሳለ እግረ መንገዱን በጤና ጣቢያው ደጃፍ አልፎ ለመሄድ አሰበና አቅጣጫውን ወደዚያ አመራ፡፡ በጤና ጣቢያው ውስጥ ሮዝና ሙሶንዳ ልጆቹን በመንከባከብና በማስተማር ሲረዱ ተመለከተ፡፡ ቺሽምባን ሲመለከቱ ልጃገረዶቹ ምን እንደተከሰተ ለማወቅ ጓጉተው ነበር፡፡ "እንዴት ሆናችሁ?" በማለት ጠየቁት፡፡

"ጎዲዊን ጥረት አደረገና ተሳካለት፥ አሁን ያለው እዚያ ነው፡፡ አቶ ቺዩሱ ሊፈትኑት የፈለጉ ይመስላል፡፡" በማለት ቺሽምባ መለሰላቸው፡፡

ልጃገረዶቹ ከልጆቹ ጋር ወደ ጀመሩት እንቅስቃሴዎች ተመለሱ፡፡ "ሌሎችን መረዳት ጥሩ ነገር ነው፡፡" የሚል ነበር የቺሽምባ ሀሳብ፥ መንገዱን እያቆራረጠ ወደ ቤቱ በመሄድ ላይ ሳለ፣ ደስ ስላለው እያፏጨ ነበር፡፡

**ተግባር** 1

አስጠኚችሁ የጥናት ቡድኑን በጥንድ በጥንድ ትከፍላችኋለች/ይከፍላችኋል፡፡ በየተራ አንዳችሁ ለሌላችሁ ጥሩ አድርጋችሁ አንብቡ፡፡

**ተግባር** 2

አስጠኚችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል ፡፡ ጥያቄዎቹ ላይ ከተወያያችሁ በኋላ መልሱን በግላችሁ ፃፉ፡፡

1.ቺሽምባና ጎዲዊን በጠዋት የሄዱት የት ነበር?

______________________________

2. ወደ ገበያው በቀረቡ ቁጥር የምን ድምጽ ሰሙ?

______________________________

3. አቶ ቺዩሱን ለመግለጽ የተጠቀሙበት ቃል ምን የሚል ነበር?

______________________________

4. ልጆቹ ጋራዡ አጠገብ ሲደርሱ አቶ ቺዩሱ ምን እያደረጉ ነበር?

______________________________

5. ጎዲዊን ምን ተሰማው?

_______________________________________________

6. ጎዲዊን በጋራዥ ውስጥ ለሚያደርገው እገዛ አቶ ቺየሱ መክፈል ይችሉ ነበር?

_______________________________________________

7. ጎዲዊን ስራውን የጀመረው መቼ ነበር?

_______________________________________________

8. ቺሽምባ ሊሄድ ሲል ለጎዲዊን በጆሮው የነገረው ቃል ምን የሚል ነበር?

_______________________________________________

9. ቺሽምባ ወደ ቤቱ ሲመለስ እግረ መንገዱን ያለፈው በየት በኩል ነበር?

_______________________________________________

10. ከማን ጋር አወራ?

_______________________________________________

11. ቺሽምባ ወደ ቤቱ ሲመለስ ምን አሰበ?

_______________________________________________

**ተግባር 3**

አሁን ደግሞ አስጠኛችሁ መልመጃዎችን ታነብላችሁ/ያነብላችሁና ትክክለኛውን መልስ እንድታ ከቡ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል።

1. “ ፊቱ በደስታ ፈካ ” ማለት

ሀ. ፊቱ እሳት ላይ ነበር።

ለ. በአይኑ ላይ ንዴት ይታይ ነበር።

ሐ. በጣም ደስተኛ ስለሆነ ፊቱ ላይ ይታይ ነበር።

2. “ ለመናገር ድፍረት አገኘ ” ማለት

ሀ. ጮክ ብሎ ተናገረ።
ለ. ፍርሀቱን ወደ ጎን በመተው ተናገረ።

ሐ. ማለት የፈለገውን ነገር አስታወሰና ተናገረ

3. አቶ ቺዬሱ ጎዲዊንን “ ለመፈተን ” ፈለጉ፡፡ ይህ ማለት

ሀ. የጽሁፍ ፈተና ለመስጠት ፈለጉ፡፡

ለ. ለጊዜው ከጎዲዊን ጋር አብሮ ለመስራትና እንዴት እንደሚሰራ ለማየት ፈለጉ፡፡

ሐ. ጎዲዊንን ብዙ ጥያቄዎች ለመጠየቅና እንዴት እንደሚመልስ ለማየት ፈለጉ፡፡

**ተግባር** 4

ከታች የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን እንድትሰሩ አስጠኚያችሁ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ለማጽዳት | መከራከር | እፈልግ | ስለጓጓ | እንጉርጉሮ |
| የፈራን | ድፍረት | ጓጓች | ለማፏጨት | የሸመገሉ |

**ተግባር** 5

ከላይ የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች አሟሉ፡፡

1. ለአንድ አመት ያህል ከቤቷ ውጭ በመቆየቷ ወደ ቤቷ ለመመለስ ________________________________ ፡፡

2. በገበያ ላይ የአንድን እቃ ዋጋ ዝቅ ለማድረግና ለመግዛት ስንፈልግ ዋጋው ላይ ______________________________ እንችላለን፡፡

3. ትንሹ ልጅ ____________________ ሲሞክር ከአፉ የሚወጣው አየር ብቻ ነው፡፡

4. ______________ ሰዎች አውቶቡስ በሚሳፈሩ ጊዜ የሰው እርዳታ ያስፈልጋቸዋል፡፡

5. ውሻ ያለበት ቦታ __________________________ መስለን መታየት የለብንም፡፡

6. አንድ ሰው እውነቱን ለመናገር ሁል ጊዜ ________________ ሊኖረው ይገባል፡፡

7. ንቦች እንዴት እንደሚኖሩ ለማየት ____________ ወደ ንብ ቀፎው እንደተጠጋ በንብ ተነደፈ፡፡

8. የቆሸሹትን ብረት ድስቶች ያለሳሙና ________________________ አስቸጋሪ ነው፡፡

9. አያቴ የቆዩ ዘፈኖችን __________________________ ስትሰማ እንባ ይተናነቃታል፡፡

10. ወደ ሲኒማ አብሬው ለመሄድ __________________________ እንደሆነ ጠየቀኝ፡፡

**ተግባር** 6

**በዚህ ትምህርት ውስጥ ስለአነበባችሁት ሁለት ወይም ሶስት አረፍተ ነገሮችን ፃፉ::**

# ትምህርት 12

# ቺሽምባን መርዳት

**አስጠኛችሁ ታሪኩን ስታነብላችሁ/ሲያነብላችሁ በደምብ ተከታተሉ::**
**አዲስ ወይም አስቸጋሪ ሆነው ያገኛችሁትን ቃል ከስሩ አስምሩበት::**

---

ላለፉት ጥቂት ሳምንታት በትምህርት ቤት ዝግ ሮዝ ከወ/ሮ ሙሊንጋና ከአቶ ሙሊንጋ ቤተሰ ቦች ጋር ባሳለፈችበት ጊዜ ውስጥ በርካታ ነገሮች ተከስተዋል:: እሷና ሙሶንዳ ዘወትር ሰኞ እለት በጤና ጣቢያው ውስጥ እገዛ መስጠታቸውን ቀጥለዋል:: ጎዲዊን በየቀኑ በጋራዥ ውስጥ ይሰራል::

ሙሶንዳ በተጨማሪ በመንደራቸው ውስጥ በሚሰጠው የመጀመሪያ እርዳታ ስልጠና ላይ ከእናቷ ጋር በመሆን እየተሳተፈች ነው:: በቤታቸው ውስጥ አንድ ሰው ሲጎዳ ምን ማድረግ እንዳለባት እየተማረች ነው::

አንድ ቀን ጎዲዊን እጁን በአሮጌ ጨርቅ ጠቅልሎ ወደ ቤቱ መጣ:: የህመም ስሜት እንዳለበት ከፊቱ ላይ ይነበብ ነበር::



“ እጅህን ምን ሆንክ? ” ጠየቀችው ሙሶንዳ ::

“ ጥቂት ስራዎችን በመስራት ላይ እያለሁ ቆረጥኩት:: አቶ ቺዬሱ ወደ ጤና ጣቢያ እንድሄድ ፈልገው ነበር:: ነገር ግን እቤታችን ውስጥ ነርስ እንዳለ ነገርኳቸው::” አለ ሙሶንዳ ላይ ፈገግ እያለ:: ወ/ሮ ሙሊንጋ ጨርቁን ከጎዲዊን እጅ ላይ እያስወገዱ “ቁስሉ ጥልቅ አይደለም÷ሆኖም ግን ቆሻሻ ይዟል::” በማለት አስተያየታቸውን ሰጡ:: ሙሶንዳ ውሃና ሳሙና አመጣችና አዲሱን ችሎታዋን በመጠቀም ቁስሉን አፀዳች::

“ ወይኔ እጄን!” በማለት ጎዲዊን ጮኸና እጁን መነጨቃት:: በዚህን ጊዜ ሙሶንዳ እንዳሳመመ ችው ተረዳች::

ቺሽምባ ወደ ቤቱ ሲሄድ እግረ መንገዱን ሰላም ሊላቸው ወደ ቤታቸው ጎራ ሲል ጎዲዊን ጮክ ብሎ ሲናገር ስለነበር ሰማው:: “ነርሷ አስቸጋሪ ከሆነ በሽተኛ ጋር እየሰራች መሆኑ ይታየኛል!” አለ::ሙሶንዳ የወንድሟን እጅ ወደ ሞቀው ውሀ ጎትታ ካስገባችው በኋላ ቀስ ብላ አጠበችለት::

ከጥቂት ጊዜ በኋላ አቶ ሙሊንጋ ከእርሻ ስራቸው ወደ ቤት ተመለሱ፡፡ ሌሎቹን የቤተሰብ አባላት ግቢያቸው ከሚገኝ አንድ የዛፍ ጥላ ስር ተቀምጠው ስላገኟቸው፥ እሳቸውም በርጩማ አውጥተው በመቀመጥ ተቀላቀሏቸው፡፡ “ ቺሽምባ ፥ እራት አብረን እንድንበላ አትቆይም?” በማለት ወ/ሮ ሙሊንጋ ጠየቁት፡፡ ቺሽምባም ግብዣውን በደስታ ተቀበለው፡፡

በዚያን እለት ምሽት ከእራት በኋላ ቤተሰቡ በእሳት ዙሪያ ተቀምጠው ነበር፡፡ እያንጻንጻቸው ያወራሉ፥ ቺሽምባ እንደማያወራ ጎዲዊን ተመለከተና “ቺሽምባ !ለምንድን ነው ዝም ያልከው?” ሲል ጠየቀው፡፡

“አዝናለሁ፥” በማለት ቺሽምባ መለሰ፡፡ “ ስለ ትምህርቴ እያሰብኩ ነበር፥ ምን ያህል ወደኋላ እንደምቀር፡፡ ለመጨረስ ሁለት አመታት ብቻ ያስፈልገኛል፡፡ እስካሁን ድረስም ስራ አላገኘሁም ፡፡ ትምህርት ቤቱ በሚገኝበት ካብዌ ዘመዶች ቢኖሩኝ ኖሮ የቤት ኪራይ ሳልከፍል አብሬአቸው እኖር ነበር፡፡ ነገር ግን ማንንም ሰው አላውቅም፡፡ ጥረት ማድረግ እንደሚገባኝ ባለማቋረጥ እያሰ ብኩ ነው፥ ሆኖም ግን በአሁኗ ሰዓት ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም፡፡”

በዚህን ጊዜ  ሁሉም በዝምታ ተዋጡ፡፡ ወ/ሮ ሙሊንጋ ድንገት አንድ ሀሳብ መጣላቸው፡፡ “በካብዌ የሚኖር አንድ የአክስቴ ልጅ አለ፡፡”ሲሉ ተናገሩ፡፡ “ደብዳቤ ልልክለትና ከእሱና ከቤተሰቡ ጋር አብረሀቸው መቆየት እንደምትችል ልጠይቀው እችላለሁ፡፡”

“ያ ችግሩን በከፊል ያቀለዋል፥ ነገር ግን ሌሎችንስ ወጪዎች እንዴት ይሸፍናቸዋል?” ጠየቀች ሮዝ ፡፡

“በጥንቃቄ ልታስብበት የሚገባህ ክፍል ያንን ነው፥ ልጅ ቺሽምባ ፡፡” አሉ አቶ ሙሊንጋ ፡፡ ቀጥለውም “አንተ ብልህና ጠንካራ ሰራተኛ ነህ፡፡ አንድ ልትሰራው የምትችለው ነገር ብታገኝ ምናልባትም ትምህርት ቤቱ ከመከፈቱ በፊት ባሉት ሳምንታት ውስጥ በቂ ገንዘብ ልታገኝ ትችል ይሆናል፡፡ መጨረሻ ላይ ትንሽ ቢጎድልብህ እንኳ እኔ ላበድርህ እችላለሁ፡፡”

“አባቴ አንድ አባባል አለው፥ አንድ ሰው ገንዘብ ማግኘት ከፈለገ ሰዎች የሚፈልጉት ሆኖ ነገር ግን ማንም ሰው የማያቀርብላቸውን ነገር ማሰብና እዚያ ላይ መስራት ነው፡፡” አለች ሮዝ በማከል፡፡

ቺሽምባ የተስፋ ጭላንጭል ታየው፡፡ “ጥሩ ሀሳቦችን ለግሳችሁኛል” በማለት ተናገር፡፡ “እስቲ አስብበትና ምን ማድረግ እንደሚገባኝ አያለሁ፡፡”

**ተግባር** 1

**አስጠኛችሁ የጥናት ቡድኑን በጥንድ በጥንድ ትከፍላችኋለች/ይከፍላችኋል፡፡ በየተራ አንዳችሁ ለሌላችሁ ጥሩ አድርጋችሁ አንብቡ፡፡**

**ተግባር** 2

**አስጠኛችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል ፡፡ ጥያቄዎቹ ላይ ከተወያያችሁ በኋላ መልሱን በግላችሁ ፃፉ፡፡**

1. **ሮዝ የትምህርት ቤት ዝጉን ከሙሶንዳ ቤተሰብ ጋር ለማሳለፍ ለምን ወሰነች**?

______________________________________________

2. **በመንደሩ ውስጥ ሲካሄድ የነበረው ስልጠና ምንድን ነበር**?

______________________________________________

3. **ከዚህ ስልጠና ሙሶንዳ ምን ተማረች**?

______________________________________________

4. **የጎዲዊን እጅ ምን ሆነ**?

______________________________________________

5. **ወደ ጤና ጣቢያ ያልሄደው ለምንድን ነበር** ?

______________________________________________

6. **ለምንድን ነው ቺሽምባ ሙሶንዳን አስቸጋሪ ከሆነ በሽተኛ ጋር እየሰራች እንደሆነ ይታየኛል ያላት**?

______________________________________________

7. **አቶ ሙሊንጋ ከእርሻ ስራቸው እቤታቸው እንደተመለሱ ምን አደረጉ**?

______________________________________________

8. **እራታቸውን ከበሉ በኋላ ቺሽምባ ያላወራው ለምንድን ነው**?

______________________________________________

9. **ትምህርት ቤት ተመልሼ ልገባ አልችል ይሆናል ሲል ቺሽምባ ያሰበው ለምንድን ነው**?

______________________________________________

10. የወ/ሮ ሙሊንጋ ሀሳብ ምን ነበር?

---

11. አቶ ሙሊንጋ በጥንቃቄ እንዲያስብበት ለቺሽምባ የነገሩት ምን ነበር?

---

12. አባቴ ገንዘብ ሊገኝ ስለሚችልበት መንገድ አንድ ጥሩ አባባል አለው ያለችው
ሮዝ ምንድን ነው?

---

**ተግባር** 3

አሁን ደግሞ አስጠኛችሁ መልመጃዎችን ታነብላችሁ/ያነብላችሁና ትክክለኛውን መልስ እንድታ ከቡ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡

1. " ትንሽ ቢጎድል " ማለት
   ሀ. በበቂ ቁመት ሳያድግ ሲቀር
   ለ. የሚፈለገውን ያህል ባይገኝ
   ሐ. ያልተረፈ ነገር ግን በቂ ሲገኝ

2. ቺሽምባ ሲናገር " ምን ማድረግ እንደምችል አያለሁ" ሲል ምን ማለቱ ነው?
   ሀ. ሊሰራ የሚችለው ነገር ካለ ለመሞከር ያስባል፡፡
   ለ. ለጥቂት ቀናት እራሱን ይጠብቃል፡፡
   ሐ. ስለ ተሰጥዖዎቹ ያስባል፡፡

**ተግባር** 4

ከታች የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን እንድትሰሩ አስጠኚያችሁ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ለመሳተፍ | ጥልቅ | በጥንቃቄ | አበድርሃለሁ | የግብዣ |
| ደብዳቤ | ይሰጣል | ስለተጎዳ | ጠቀለለች | ቤተዘመዶች |

**ተግባር** 5

**ከላይ የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች አሟሉ።**

1. **ይህ መጽሐፍ ስለ ልጆች አመጋገብ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን** ____________________ ።

2. **በስልጠናው ላይ** ______________________ **ከፈለጉ ስምዎትን በዚህ ወረቀት ላይ ይፃፉ።**

3. **ወጣቶቹ ማህበረሰቡ በሚያደረገው ስብሰባ ላይ የሚነበብ** ___________________ **ላኩ።**

4. **አየሩ ቀዝቃዛ ስለሆነ ልጇን በሚሞቅ ብርድ ልብስ** ______________________________ ።

5. **እህቴ ዛፍ ስትወጣ ሳለ እግሯ** ___________________________ **ወደ ጤና ጣቢያ ሄደች።**

6. **በሚቀጥለው እሁድ ለሚፈጽመው ጋብቻ ስነ-ስርዓት ላይ እንድትገኝ ለእህቱ** __________________________**ጥሪ ካርድ ላከላት።**

7. **በመንደራችን ውስጥ የተቆፈረው አዲስ የውሀ ጉድጓድ** _____________ **ስለሆነ ጥሩ ውሀ እያገኘን ነው።**

8. **ብዕሬን ለጊዜው** ____________________ ፥ **ነገር ግን ከተጠቀምክበት በኋላ ትመልሳለህ።**

9 **እናትየዋ የተኛችውን ልጇን ሳትቀሰቅስ** ____________________________ **በብርድ ልብስ ጠቀለለቻት።**

10. **ከትልቅ ቤተሰብ የተወለደች ስለሆነ ብዙ** _______________________________ **አሏት።**

**ተግባር** 6

**ቺሽምባ ገንዘብ ሊያገኝ የሚችልበትን መንገዶች ዘርዝሩ።**

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

# ትምህርት 13

## ማረጋገጫ


**አስጠኛችሁ ታሪኩን ስታነብላችሁ/ሲያነብላችሁ በደምብ ተከታተሉ፡፡**
**አዲስ ወይም አስቸጋሪ ሆነው ያገኛችሁትን ቃል ከስሩ አስምሩበት፡፡**

---

አንድ ቀን በማለዳ ለእናቱ አሳ ለመግዛት ቺሽምባ ወደ ገበያ ሄደ፡፡ ለመማሪያ የሚሆነውን ገንዘብ እንዴት ማግኘት እንደሚችል ለበርካታ ቀናት ሲያስብበት ነበር፡፡ የሚሸጠውን እህል ለመዝራት አሰበ፥ ነገር ግን የመዝሪያ ወቅት አልፏል፡፡ በመንገድ ዳር ላይ ከሰል ለመሸጥ አሰበ ይህንንም ብዙ ሰዎች እያደረጉት ነው፡፡ "ሌሎች ሰዎች የማይሰሩትን ነገር አስብ" የሚለውን የሮዝን ምክር አስታወሰ፡፡

የወ/ሮ ሙሶሌ አሳ መሸጫ መደብር አጠገብ እንደደረሰ ሴትየዋ አለመኖራቸውን ደረሰበት፡፡ "አሳ ለማምጣት ወደ ከተማ ሄደዋል" አሉ በሚቀጥለው መደብር ያሉ ሴትዮ፡፡ አቶ ቺዬሱም የመኪና መለዋወጫ ለመግዛት ወደ ከተማ እንደሚሄዱ ያውቅ ነበር፡፡

ይህ አንድ ሀሳብ ሰጠው፡፡"ምናልባትም እኔ ወደ ከተማ ልላክላቸውና የሚፈልጉትን ነገር ማምጣ ት፡፡እነሱ ወደ ከተማ በሚሄዱ ጊዜ ገንዘብ አያወጡም፥ እዚህም ያለው ገበያ አይመለስባቸውም ፡፡"



በዚያን ምሽት ቺሽምባ ከቤተሰቡ ጋር በጉዳዩ ላይ ተማከረ፥ ቤተሰቡም ሀሳቡን ወደዱለት፡፡ በሚቀጥለው ቀን ወደ ገበያ ተመልሶ በመሄድ ወ/ሮ ሙሶሌና አቶ ቺዬሱን አናገራቸው፡፡"ሁለታችሁም ወደ ከተማ ለመሄድ ለአውቶቡስ የምትከፍሉትን ገንዘብ ለእኔ ብትሰጡኝ ግማሹን በአውቶቡስ ለምመላለስበት እከፍልና የተቀረውን ግማሽ ትምህርቴን ለመቀጠል አውለ ዋለሁ፡፡"መሞከሩ ይበጃል በማለት ከሁለት ቀናት በኋላ ተመልሶ እንዲመ ጣ ነገሩት፡፡ "ይህ ሀሳብ በደምብ የሚሰራ ከሆነ" አሉ አቶ ቺዬሱ "ስራ ለራስህ ፈጠርክ!"

መልካሙን ዜና ለወላጆቹ ለመንገር ወደ ቤቱ በመሄድ ላይ ሳለ እግረ መንገዱን ወደ ጎዲዊን ቤተሰቦች ቤት ጎራ አለ፡፡ እቅዱን ሊያካፍላቸው ጓጉቶ ነበር፡፡ ታሪኩን ካጻመጡ በኋላ ወ/ሮ

ሙሲንጋ በተጨማሪ ሌላ ጥሩ ዜና አበሰሩለት፡፡ ከትላንት በስቲያ አቶ ሙሲንጋ ወደ ካብዌ መሄድ ስለነበረበት በዚያውም የአክስቴን ልጅ አናግሮት ነበር፡፡ ከቤተሰቡ ጋር አብሮ እንደሚ ኖርና ቤት ያፈራውን አብሯቸው እንዲመገብ ቺሽምባን ተቀብለውታል ሲል ነገረኝ፡፡ትምህርት ቤቱ ከመኖሪያ ቤታቸው አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ይርቃል በማለት ለቺሽምባ በተጨማሪ አብራሩለት፡፡ “ለምታድርበትና ለምትመገብበት ውለታ” አሉ ወ/ሮ ሙሲንጋ “በእርሻ ስራ ላይ ትረዳቸዋለህ፡፡”

“ያ ድንቅ ነው!” አለ ቺሽምባ ፡፡ “አመሰግንዎታለሁ ወ/ሮ ሙሲንጋ ፡፡”

“ቺሽምባ” አሉ አቶ ሙሲንጋ “በቅርቡ ጥቂት ገንዘብ የሚኖርህ ይመስላል፡፡ ለትምህርት ቤትህ እያጠራቀምክ መሆኑን ማረጋገጥ አለብህ፥ ምንም እንኳ አንዳንድ ጊዜ ማጠራቀም አስቸጋሪ ቢሆንም፡፡ አላስፈላጊ ለሆኑ ነገሮች ገንዘብህን ማባከን የለብህም፡፡”

“አይጨነቁ አቶ ሙሲንጋ” በማለት ቺሽምባ መለሰላቸው፥ ፊቱን በፈገግታ ሞልቶ፡፡ “ያ እንደ ማይሆን ቃል እገባሎታለሁ” ተሰናብቷቸው ዞሮ ሊሄድ ሲል ሮዝና ሙሶንዳን ተመለከተና “በሮች እየተከፈቱልኝ ነው!” አለ፡፡

**ተግባር** 1

አስጠኛችሁ የጥናት ቡድኑን በጥንድ በጥንድ ትከፍላችኋለች/ይከፍላችኋል፡፡ በየተራ አንዳችሁ ለሌላችሁ ጥሩ አድርጋችሁ አንብቡ፡፡

**ተግባር** 2

አስጠኛችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡ ጥያቄዎቹ ላይ ከተወያያችሁ በኋላ መልሱን በግላችሁ ፃፉ፡፡

1. ላለፉት ጥቂት ቀናት ቺሽምባ ስለምን እያሰበ ነበር?

____________________________________________

2. ለሽያጭ የሚሆን እህል ላለመዝራት የወሰነው ለምንድን ነው?

____________________________________________

3. በመንገድ ዳር ላይ ከሰል ላለመሸጥ የወሰነው ለምንድን ነው?

---

4. ቺሽምባ ወደ ገበያ የሄደው ለምንድን ነበር?

---

5. ወ/ሮ ሙሶሌ  የት ሄደው ነበር?

---

6. ለቺሽምባ ገንዘብ ሊያስገኝለት የሚያስችለው ሀሳብ ምንድን ነበር?

---

7. በሀሳቡ ላይ ከወላጆቹ ጋር ከተመካከረ በኋላ ቺሽምባ ምን አደረገ?

---

8. ወ/ሮ ሙሶሌና አቶ ቺዬሱ የአውቶቡስ ወጪያቸውን ከሰጡት ፥ ከተማ በተላከ ቁጥር ምን ያህል ያተርፋል?

---

9. ወ/ሮ ሙሶሌና አቶ ቺዬሱ የቺሽምባን ሀሳብ ወደውታል?

---

10.  ቺሽምባ ወደ ቤቱ ሲሄድ እግረ መንገዱን ሀሳቡን ለማን አጋራ?

---

11. ወ/ሮ ሙሊንጋ ለቺሽምባ የሚነግሩት ጥሩ ዜና ምን ነበር?

---

12. በካብዌ አብሯቸው እንዲኖር ለፈቀዱለት ቤተሰብ ውለታቸውን የሚከፍለው እንዴት ነው?

---

13. ቺሽምባ ሲሄድ ለሮዝና ለሙሶንዳ ምን አላቸው?

---

**ተግባር** 3

**አሁን ደግሞ አስጠኛችሁ መልመጃዎችን ታነብላችሁያነብላችሁና ትክክለኛውን መልስ እንድታ ከቡ  ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል፡፡**

1. አንድን ነገር “ መሞከር ከበጀ ” ይህ ማለት

ሀ. በርካታ ገንዘብ ያስወጣ ::

ለ. መሞከር ጥቅም የለውም::

ሐ. መሞከሩ ጥቅም አለው::

2. ቺሽምባ እየሄደ ሳለ “ በሮች እየተከፈቱ ነው” አለ:: ይህ ማለት

ሀ. እየሞከራቸው ያሉት ነገሮች እየተሳኩለት ነው::

ለ. ወደ ቤት ለመግባት ዝግጁ ነው::

ሐ. አንድ ነገር በሩን ከፍቶ ይዞለታል::

**ተግባር** 4

ከታች የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን እንድትሰሩ አስጠኚያችሁ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል::

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| እንድታማክረኝ | መለሰልኝ | ካገኘ | ተገፋፍቶ | ቃል ገብታልኛለች |
| ልዋጭ | ከተስማማህ | ልትመጣ | ብዙውን ጊዜ | ለመቆጠብ |

**ተግባር** 5

ከላይ የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች አሟሉ::

1. ያዋስኩትን ብዕር በወቅቱ ________________________________________ ::

2. የኤሌክትሪክ ፍጆታችንን ____________________ ከቤት ስትወጣ እባክህን መብራቱን አጥፋው::

3. በአንድ ቁና ጤፍ _________________________________ አንድ ዶሮ እሰጥሀለሁ::

4. ቀደም ብላ እንደምትመጣና ለስብሰባው የተመረጠውን አዳራሽ እንደምናዘጋጅ ____________________________ ::

5. በዚህ አመት በቂ ገንዘብ __________________________ አዲስ ቤት እንደሚሰራልን አባቴ ቃል ገብቶልናል::

6. ከመተኛቴ በፊት ____________________________________ መጽሐፍ አነባለሁ::

7. የተመገብንባቸውን ሳህኖች አንተ በጨርቅ ለማድረቅ ________________________ ፥

እኔ አጥባለሁ፡፡

8. ስራውን እርግፍ አድርጎ ለመተው ________________________ ነበር፥ ነገር ግን

በአንዳንድ ሁኔታዎች መለወጥ ምክንያት ሀሳቡን ቀየረ፡፡

9. እራት አብረን እንድንበላ ከፈለግህ ________________________ ትችላለህ፡፡

10. ስለ ወደፊት ህይወቴ ________________________ እፈልጋለሁ፡፡

**ተግባር** 6

በዚህ ትምህርት ከተማራችሁት ውስጥ ሁለት ወይም ሶስት አረፍተ ነገሮችን ፃፉ፡፡

________________________________________
________________________________________
________________________________________
________________________________________
________________________________________
________________________________________

**ተግባር** 7

ከታች የተሰጡትን ጥያቄዎች ከጓደኛችሁ ጋር በመሆን ከተወያያችሁ በኋላ ጥቅሱን በማጥናት በቃል ያዙት፡፡

**“. . . ትልቅ ጥረት አድርጉ፥ ለራሳችሁ ክቡር የሆነ ግብ ምረጡ ፡፡ ”**

1. ምን አይነት ግብ መምረጥ ይገባናል?

________________________________________

2. ግባችን ላይ ለመድረስ ምን ያህል ጥረት ማድረግ አለብን?

________________________________________

# ትምህርት 14

# የወደፊት ተስፋ

**አስጠኞቻችሁ ታሪኩን ስታነብላችሁ/ሲያነብላችሁ በደምብ ተከታተሉ፡፡**
**አዲስ ወይም አስቸጋሪ ሆነው ያገኛችሁትን ቃል ከስሩ አስምሩበት፡፡**

---



የትምህርት ቤት ዝጉ በመገባደድ ላይ ነው፡፡ ሮዝ ወደ ቤቷ በመሄድ ትምህርት ለመጀመር የምትዘጋጅበት ጊዜ ነው፡፡ ለመሄድ እየተዘጋጀች ሳለች ከሙሶንዳ ጋር እያወሩ ነበር“ ባትሄጂ እወድ ነበር፡፡ ” አለች ሙሶንዳ ፡፡

“እኔም እንደዚሁ፥” አለች ሮዝ ፡፡ “በእውነቱ ግሩም የእረፍት ጊዜ ነበር፡፡ የሆነውን ሁሉ ሳስብ ማመን ያቅተኛል፡፡ ”

“ አዎን፥” አለች ሙሶንዳ ፡፡ “ጎዲዊንን ተመልከችው ፥ ስራውን በጣም ወዶታል እናም ትምህርቱን ሲጨርስ የቴክኒክ ትምህርት ስልጠና ለመውሰድ እያሰበበት ነው፡፡ የቺሽምባ ሀሳብ በእውነቱ በደምብ ሰርቷል፡፡ የኋላ ኋላ ብዙ ደምበኞችን አፍርቶ በየቀኑ ከተማ የሚመላለስ ሰው ይሆናል፡፡

“እኛንም ተመልከች፥” አለች ሮዝ ፡፡ “ጤና ጣቢያ ውስጥ በመስራት ትልቅ ልምድ ነው ያዳበርነው፡፡

እኔም በግሌ ያረጋገጥኩት አስተማሪ መሆን እንደምችል ነው፡፡ የአካባቢያችን ምክር ቤት ያዘጋጀውና በየሳምንቱ የሚካሄድ የልጆች ትምህርት ፕሮግራም አለ ፡፡ ትምህርቱ የሚካሄደው በተለያዩ የእድሜ ክልሎች  ውስጥ ለሚገኙ ልጆች ነው፡፡ የሚቀር ልጅ የለም፥ ሁሉም ይሳተፋሉ፡፡ አሁን ስመለስ አንዱን ክፍል ለማስተማር አቅጃለሁ፡፡”

“እኔም በጤና ጣቢያው ውስጥ ማገልገሌን እቀጥልበታለሁ፥” አለች ሙሶንዳ ፡፡

“ሰኞ እለት የምሰጠውን ግልጋሎት በትምህርቴ ምክንያት መቀጠል አልችልም፥ ነገር  ግን አንዳንድ ጊዜ ከሰዓት በኋላ የማገለግልበትን ሁኔታዎች አመቻቻለሁ፡፡  ታውቂያለሽ ሮዝዬ በመጣሽበት እለት ስለ “ ማረጋገጫ ” ተነጋግረን ነበር፥ ምን ያህል ጠቃሚ ሀሳብ እንደነበርና

እንዲሁም ግንዛቤ ማግኘት እንዴት ህይወታችንን ሊቀይር እንደሚችል በመጀመሪያ አልተረዳ ሁም ነበር፡፡"

"እውነትሽን ነው፡፡"በማለት ተስማማች ሮዝ፡፡"ሁላችንም ምን ያህል እንደተቀየርን ተመልከች፥ ለዚህ ሁሉ ምክንያቱ ጥረት ማድረግንና ማረጋገጫን መጠበቅ ስለተማርን ነው፡፡"

ሙሶንዳ ፈገግ አለች፡፡ " አሁን ስትሄጂ በጣም ትናፍቂኛለሽ፥ ሮዝ " አለች፥ ከዚያም እርስ በርሳቸው ተቃቀፉ፡፡

"ልጆች፥እየረፈደ ነው፡፡" ወ/ሮ ሙሊንጋ ከውጭ ሆነው በመጣራት፡፡"ጉዞ መጀመር አለብን! "

ልጃገረዶቹን ከውጭ ሆነው ወደሚጠብቋቸው ወጥተው ሄዱ፡፡ "ቺሽምባ የታለ?" ሙሶንዳ ጠየቀች ፡፡

"ዛሬ ጠዋት የሚሰራው ነገር እንዳለ ነግሮኛል፥ ስለዚህ አውቶቡስ መናኸሪያ እናገኘዋለን፡፡" አለ ጎዲዊን ፡፡ የሮዝን ቦርሳ አንጠለጠለና ሁሉም ተያይዘው ወደ አውቶቡሱ በእግራቸው አዘገሙ፡፡ ወ/ሮ ሙሊንጋና ትንንሾቹ ልጆች ቀድመው ወጡ፥ሮዝና ሙሶንዳ በመንገድ ላይ አንዴ አንዱን አንዴ ሌላውን እያነሱ ያወሩ ነበር፡፡ አቶውቡስ የቆመበት ቦታ ሲደርሱ ሰዎች ቀደም ብለው ተሳፍረው ነበር፡፡ ቺሽምባን በአይናቸው እየፈለጉ ሳለ ከርቀት እጁን እውለበለበ ወደ እነሱ መጣ ፡፡

" ደህና ሁኚ! ሮዝ፥ ላደረግሽልኝ ነገር ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ! " አለ ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለ፥ ልክ አውቶቡስ ውስጥ ከመግባቷ በፊት ደርሶ ፡፡

ወደ ቤት በመመለስ ላይ ሳሉ ፥ ሙሶንዳ ወንዙ ዳርቻ ለመሄድ እንዲፈቀድላት ወላጆቿን ጠየቀች፡፡ ወደምትወደው ስፍራ ሄደችና ቋጥኙ ላይ ወጥታ በጀርባዋ ተንጋላ በመተኛት ሰማዩን ተመለከተች፡፡ በርካታ ሀሳቦች በአእምሮዋ ውስጥ ተመላለሱ፡፡ ስለ ትምህርት ቤት ዝግ አሰበችና የሚቀጥለው አመት ምን ድንቅ ነገሮችን ይዞ ይመጣ ይሆን በማለት ተገረመች፡፡ ነፋሻማ ቀን ነው፥ ቢጫዋን ወፍ አስታወሰች፡፡ " በምሞክረው ነገር ሁሉ እግዚአብሄር ይረዳኛል፡፡" ስትል ለራሷ አሰበች ወደ ቤቷ ለመሄድ ስትነሳ፥ ነፋሱ ከጀርባዋ እየነፈሰ በጉዞዋ ላይ ተጨማሪ ጉልበት ሰጣት ፡፡

**ተግባር** 1

**አስጠኛችሁ የጥናት ቡድኑን በጥንድ በጥንድ ትከፍላችኋለች/ይከፍላችኋል፡፡ በየተራ አንዳችሁ ለሌላችሁ ጥሩ አድርጋችሁ አንብቡ፡፡**

**ተግባር** 2

**አስጠኛችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል ፡፡ ጥያቄዎቹ ላይ ከተወያያችሁ በኋላ መልሱን በግላችሁ ፃፉ፡፡**

1. **ሮዝ ከሙሶንዳ ጋር እያወራች ምን ታደርግ ነበር**?

_______________________________________________

2. **በትምህርት ቤት ዝግ ውስጥ ስለተከናወኑት ነገሮች ልጃገረዶቹ ምን አሉ**?

_______________________________________________

3. **ጎዲዊን ትምህርቱን ሲጨርስ ምን ለማድረግ አሰበ** ?

_______________________________________________

4. **የቺሽምባ ሀሳብ እንዴት ሊሰራ ቻለ**?

_______________________________________________

5. **ሮዝ ቤቷ ከተመለሰች በኋላ ምን ለማድረግ አቀደች**?

_______________________________________________

6. **ሙሶንዳ ለጤና ጣቢያው ግልጋሎት መስጠቷን ትቀጥል ይሆን**?

_______________________________________________

7. **ሙሶንዳ ፥ ሮዝ ፥ ጎዲዊንና ቺሽምባ በትምህርት ቤት ዝግ ምን ተማሩ**?

_______________________________________________

8. **ከሮዝ ጋር ወደ አውቶቡስ መናኸሪያ አብረው የተጓዙት እነማን ነበሩ**?

_______________________________________________

9. **እዚያ ያገኛቸው ማን ነበር**?

_______________________________________________

10. ሙሶንዳ ወደ ቤቷ በመመለስ ላይ ሳለች ወዴት ሄደች?

___

11. በቋጥኝ ላይ ተንጋላ ተኝታ ሳለ ስለ ምን አሰበች?

___

12. ቢጫዋን ወፍ ለምን አስታወሰች?

___

13. ስለ ቢጫዋ ወፍ ስታስብ ስለራሷ ምን አሰበች?

___

**ተግባር 3**

አሁን ደግሞ አስጠኛችሁ መልመጃዎችን ታነብላችሁ/ያነብላችሁና ትክክለኛውን መልስ እንድ ታከቡ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል።

1. "የኋላ ኋላ ብዙ ደምበኞችን ያፈራል።" ይህ ማለት

   ሀ. ከጊዜ ብዛት በርካታ ሰዎች ከሚሰጠው አገልግሎት ተጠቃሚ ይሆናሉ።

   ለ. በርካታ ሰዎች የሚሰጠው አገልግሎት መጠቀማቸውን ያቆማሉ።

   ሐ. በአንድ ጊዜ ለአንድ ሰው ብቻ ይሰራል።

2. አውቶቡስ መሳፈሪያው ጋር ሲደርስ የቺሽምባ "ትንፋሹ ቁርጥ እያለ" ነበር። ይህ ማለት

   ሀ. ትንፋሽ አጥሮታል ማለት ነው።

   ለ. ተናዷል ማለት ነው።

   ሐ. እርቦታል ማለት ነው።

**ተግባር 4**

ከታች የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን እንድትሰሩ አስጠኚያችሁ ትጠይቃችኋለች/ይጠይቃችኋል።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ለማግባባት | ካቆየነው | ማሰብ | አመለጣት | መንገደኞች |
| ልምዶችን | የተለያዩ | እንዲያዘጋጁ | ማሳፈር | ጉልበታቸውን |

**ተግባር 5**

**ከላይ የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች አሟሉ ፡፡**

1. ከቤቷ ዘግይታ ስለወጣች አውቶቡሱ ______________________________ ፡፡
2. በመምህርነት ሙያ ለ25 አመታት ስላሳለፈች በርካታ ____________________ አካብታለች ፡፡
3. በአዘጋጀችው የአትክልት ስፍራ በርካታና __________________ አይነት አበባዎችን ተክላለች ፡፡
4. በአለማችን ላይ ጦርነት አብቅቶ በሰላም ስለሚኖርበት ጊዜ ____________ ትችላለህ ?
5. ለተጨማሪ አንድ ሰዓት ቆይተን ሰዎችን ባቡሩ ላይ _______________ አንችልም፡፡
6. መጽሐፉን በጣም ስለወደደው እኔም እንዳነበው ________________________ ብዙ ጥረት አደረገ ፡፡
7. የተጋጨውን መኪና ወደ ዳር ለማውጣት ________________________ ጨረሱ፡፡
8. ከአውቶቡሱ ላይ በርካታ ____________ በስህተት ካልፈለጉበት ፌርማታ ላይ ወረዱ ፡፡
9. ለጥቂት ቀናት __________ ቲማቲሙ ይበስላል ፡፡
10. ወንበሮቹን በደምብ ____________ አስተማሪው ተማሪዎቹን ጠየቀ ፡፡

**ተግባር 6**

**የሚከተለውን ጥቅስ በቃል ያዙ፡፡**

> **“ከፀሀይዋ ስር ካለው ስፍራ ቦታህን ለመያዝ ጥረት አድርግና ከአብረቅራቂው ብርሃንዋ በቂ ድርሻህን ተቀበል፡፡”**